# የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

# የወጡ ደንቦችና መመሪያ

ህዳር 2003
አዲስ አበባ



## ማውጫ


የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌደሬሽን መተዳደሪያ ውስጠ ደንብ

የክለቦች ማሚያ መመሪያ

የአካላት የስነምግባር መመሪያ

የድጋፍና ሽልማት አሰጣጥ መመሪያ

የአትሌቶች መምረጫ እና የአሰልጣኞች ደረጃ መስጫ መስፈርት መመሪያ

የአትሌቶች የውጭ ውድድር ጉዞ እና የአትሌት ማናጀሮች አሠራር መመሪያ

# የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

## መተዳደሪያ ውስጠ ደንብ

## መግቢያ

በአለም አቀፉ የስፖርት ህግ መሠረት በአንድ ሀገር በአንድ የስፖርት ዓይነት ሊኖር የሚችለው አንድ ሀገር አቀፍ ፌዴሬሽን ብቻ በመሆኑ ፌዴሬሽኑ የሀገሪቱን ሕግና ደንብ ጠብቆ በሕዝብ፣ በመንግስትና በድርጅቶች ድጋፍ የሚንቀሳቀስ ሀገር አቀፍ፣ አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ አትሌቲክስ ተግባራትን የሚያከናውን የስፖርት ማህበር ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም፤ ፌዴሬሽኑ ሕዝባዊ አደረጃጀቱን አጠናክሮ፣ ነፃ አሠራርን በማስፈን፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ተልዕኮውን በተሟላ መልኩ እንዲያከናውንና ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቱን አውቆ እንዲመራ ለማድረግ እንዲሁም፤

1. የአትሌቲክስ ስፖርት የደረሰበትን ደረጃ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት
2. በአዲስ መልክ ከተጠናው የBPR ጥናት አንፃር ደንቡ መቃኘት ስላለበት እና
3. አገራችን ከያዘችው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አንፃርም በአትሌቲክስ ስፖርትም መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱና፤

በስፖርት ኮሚሽን የስፖርት ማህበራትን ስለሚቋቋምበት ሁኔታ ለመወሰንና ለማደራጀት  በወጣው የሀገር አቀፍ ፌዴሬሽኖች ማቋቋሚያ መተዳደሪያ ደንብና በአለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሕግ መሠረት ይህ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን መተዳደሪያ ደንብ በ4 ክፍሎች ማለትም፡-

ክፍል አንድ ጠቅላላ
ክፍል ሁለት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም ስለአባልነት
ክፍል ሦስት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አቋምና አደረጃጀት
ክፍል አራት ልዩ ልዩ ጉዳዮችን አካቶ ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>
## <u>ጠቅላላ</u>
### አንቀፅ አንድ
### ስለመቋቋም

የስፖርት ኮሚሽን የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን በ2000 ዓ.ም. በወጣው መመሪያ አንቀፅ 9.1.15 እና አንቀፅ 9.6.5/መ እንዲሁም በአለም አቀፉ የአትሌቲክስ ፌዴሽኖች ማህበር ህግ መሰረት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ስፖርትን በበላይነት የሚመራ የኢትዮጵያ አትሌቲክሰ ፌዴሬሽን በሚል ስያሜ ህጋዊ አካል ሆኖ ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሟል፡፡

### አንቀፅ ሁለት
### አውጭው አካል

ከላይ በአንቀጽ አንድ በተጠቀሱት ህግና ደንቦች መሰረት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ ይህን መቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ አውጥቷል፡፡

### አንቀፅ ሦስት
### አጭር ርእስ

ይህ ደንብ የተሻሻለው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መቋቋሚያና መተዳደሪያ ውስጠ ደንብ ቁጥር 1/2003 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀፅ አራት
### ትርጓሜ

1. "ኮሚሽን" ወይም ኮሚሽነር ማለት እንደቅደም ተከተሉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ስፖርት ኮሚሽን ወይም ኮሚሽነር ማለት ነው፡፡
2. "የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን" ማለት የአትሌቲክስ ስፖርት በመላ ሀገሪቱ ለማስፋፋትና ለመምራት በሕግ ኃላፊነት የተሰጠው አካል ማለት ነው፡፡
3. "አለም አቀፍ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን" ማለት የአትሌቲክስ ስፖርትን በአለም አቀፍ ደረጃ በበላይነት የሚመራ አካል ነው፡፡
4. "የክልል ፌዴሬሽን (የክልል ስፖርት አመራር)" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ አዲስ አበባንና ድሬደዋ አስተዳደርን ጨምሮ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ወይም የስፖርት አመራር ማለት ነው፡፡
5. "ክለብ" ማለት የአትሌቲክስ ስፖርት እንቅስቃሴን ለማራመድ የተቋቋመ ማኅበር ነው፡፡
6. "የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ" ማለት የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን በወጣው መመሪያ መሠረት የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፡፡
7. "የአትሌቲክስ ስፖርት" ማለት የመም፣ የሜዳ ተግባራት፣ የጐዳና ላይ ሩጫ፣ የርምጃ፣ የአገር አቋራጭና የተራራ ላይ ሩጫን ያካተተ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ማለት ነው፡፡
8. "አገር አቀፍ ውድድር" ማለት ከአንድ ክልል በላይ የሚሳተፉበት የአትሌቲክስ ውድድር ነው፡፡
9. "ኢንተርናሽናል ውድድር" ማለት ከአንድ አገር በላይ የሚሳፈፉበት የአትሌቲክስ ውድድር ነው፡፡
10. "የአትሌት ማናጀር" ማለት (የአትሌቶች ወኪል በመሆን ከIAAF እና ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ህጋዊ እውቅና ያለው ነው፡፡
11. "የክብር አባል" ማለት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አቅራቢነት በስፖርቱ ዙሪያ ባበረከቱት አስተዋፅኦ ምክንያት የሚሰየም ሰው ማለት ነው፡፡
12. "ኢመርጀንሲ ኮሚቴ" ማለት በ2 የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች መካከል አስቸኳይ ጉዳዮችን አከናውኖ በሚቀጥለው ስብሰባ አቅርቦ የሚያስወስን በጠቅላላ ጉባኤ አማካይነት ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት መካከል የሚሰየም አካል ነው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም ስለ አባልነት</u>

### አንቀፅ አምስት

### ዓላማ

ከአጠቃላይ የህብረተሰቡ አትሌቲክስ ስፖርት እንቅስቃሴ በመነሳት በተለይ የወጣቱን ትውልድ ግንዛቤና ተሳትፎ በማጠናከር የላቀ ችሎታ ያላቸው ምርጥ ስፖርተኞች እንዲፈሩ በማድረግ በአለም አቀፍ ደረጃ የአገራችንን ተወዳዳሪነትና ተጠቃሚነት ማስፋት፡፡

### አንቀጽ ስድስት

### የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌደሬሽን ስልጣንና ተግባር

1. የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙብት ሁኔታ ለመወሰን በወጣው ማቋቋሚያ መመሪያ እንዲሁም በአለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኖች ማህበር ሕገ ደንብ መሠረት በሀገሪቱ ውስጥ የአትሌቲክስ ስፖርትን በበላይነት ይመራል፣ ስለማስፋፋት ሁኔታ ስልቶችን ይቀይሳል፤
2. ስፖርቱን በሚመለከት የመንግስት ፖሊሲን፣ ሕግን፣ ደንብንና መመሪያዎችን ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፤
3. ደረጃቸውን የጠበቁ የአትሌቲክስ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲቋቋሙ ይደግፋል ዕውቅና ይሰጣል፤
4. የአትሌቲክስ ስፖርትን የሚመለከቱና ተዛማጅ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፤
5. በሀገር ውስጥ ከአንድ ክልል በላይ በሚያሳትፍ፤ በአለም አቀፍ ደረጃ ከአንድ ሀገር በላይ የሚደረጉ የአትሌቲክስ ውድድሮችን ያካሂዳል፣ ፈቃድ ይሰጣል፤
6. የስፖርት ክለቦች ስለሚደራጁበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፣ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤
7. የታዳጊ፣ የወጣቶችና የሴቶች ተሳትፎ ስለሚያድግበት ሁኔታ ስልት ይቀይሳል፤
8. ምርጥ አትሌቶች እንዲፈሩና ዘመናዊ ስልጠና እንዲያገኙ ስልት ይቀይሳል፤
9. ከአለም አቀፍና ከሀገር ውስጥ የአትሌቲክስ ተቋማት ጋር በመተባበር ኮርሶችን፣ ሴሚናሮችን፣ ወርክሾፖችንና ስልጠናዎችን ያዘጋጃል፣ ዕውቅና ይሰጣል፤
10. የአትሌቲክስ ስፖርቱን በሚመለከት በአህጉራዊና አለም አቀፋዊ ስብሰባዎች ላይ ይሳተፋል፣ የተላለፉ ውሳኔዎችንም ተግባራዊ ማድረግ፤
11. የአሰልጣኞችንና የዳኞችን የመመልመያ መስፈርት ያዘጋጃል ደረጃ ያወጣል ፈቃድ ይሰጣል፤
12. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልልም ሆነ በፌደራል ደረጃ ስፖርቱ እንዲስፋፋ ድጋፍ ያደርጋል፤
13. የአትሌቲክስ ስፖርቱን ለማሳደግ በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ መሰማራትና የገቢ ማስገኛ ተቋማትን ያቋቁማል፤
14. የኦሎምፒክ ጨዋታዎችን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ጋር በመተባበር ይሰራል፤
15. ለኮሚሽን መ/ቤቱ በየጊዜው (በየሩብ ዓመቱ) የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ፤
16. የውስጥ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች የማውጣትና በጠቅላላ ጉባኤ በማስፀደቅ፣ በሥራ ላይ ማዋል፤
17. ኢትዮጵያ የተቀበለችውን የፀረ-ዶፒንግ ኮንቬንሽን ያከብራል ያስከብራል፤
18. በክልሎች ፌዴሬሽኖች እንዲደራጁ ድጋፍ ያደርጋል፣ እውቅና ይሰጣል፣ መመሪያ ያወጣል፤
19. በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ የላቀ አስተዋፅዖ ላበረከቱ ሰዎችና አካላት በተለያዩ መንገዶች ዕውቅና ይሰጣል፤
20. በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ ለሚነሱ አለመግባባቶችና ክርክሮች ዳኝነት ይሰጣል፤
21. በአመት አንድ ጊዜ የፌዴሬሽኑን የጠቅላላ ጉባኤ ያካሂዳል፤
22. ከስፖርት ጋር በተያያዙ የበጎ አድራጎት ተግባራት ላይ ይሳተፋል፡፡
23. ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል፣ ይከሰሳል፡፡

### አንቀፅ ሰባት

### አባልነት

1. የኢ.አ.ፌ. የሚቋቋመው የክልልና የከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽኖች በሚመሰርቱት ህብረት ሆኖ ለአባልነትም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የስፖርት ኮሚሽን የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙብት ሁኔታ ለመወሰንና ለማደራጀት በወጣው መመሪያ መሰረት የተቋቋሙ የክልሎችና የከተማ አስተዳድሮች ብቻ ይሆናሉ፡፡
2. የኢ.አ.ፌ. አባል የሚሆነው ፌዴሬሽን ከእያንዳንዱ ክልል ወይም ከተማ አስተዳድር የአትሌቲክስ ስፖርትን በበላይነት የሚመራው አንድ ፌዴሬሽን ብቻ ይሆናል፡፡

3. የአባልነት ምዝገባን በሚመለከት የክልሉ ወይም የከተማው አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የኢ.አ.ፌ. አባል ለመሆን በቅድሚያ ለቀጣዩ ጉባኤ በአጀንዳ ተይዞ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጥያቄውን/ማመልከቻውን ለኢ.አ.ፌ. ጽ/ቤት በፅሁፍ ያቀርባል፡፡ ማመልከቻውም፡-

ሀ. የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት አድራሻ፣

ለ. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ስፖርት ኮሚሽን የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰንና በወጣው መመሪያ መሰረት የተቋቋመበትን የመተዳደሪያ ደንብ፣

ሐ. የተመረጡ የስራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላትን ስም ዝርዝር፣

መ. በስሩ የተመዘገቡ የክለቦችን፣ የአሰልጣኞችን፣ የአትሌቶችንና የዳኞችን ዝርዝር፣

ሠ. በክልሉ የአትሌቲክስ ስፖርት የደረሰበትን ደረጃ የሚያሣይ ሪፖርት መያዝ ይኖርበታል፡፡

4. እያንዳንዱ የክልል/የከተማ መስተዳድር ፌዴሬሽን የኢ.አ.ፌ አባል ሆኖ ሲመዘገብ የኢ.አ.ፌ. ጠቅላላ ጉባኤ በሚያሳልፈው ውሳኔ መሰረት ዓመታዊ የአባልነት መዋጮ ክፍያ ይፈፅማል፡፡

5. በመጨረሻም የኢ.አ.ፌ. ጠቅላላ ጉባኤ ጥያቄውን መርምሮ ሲያፀድቀው በአባልነት ይመዘገባል፡፡

6. ሁሉም አባል ፌዴሬሽኖች በኢ.አ.ፌ. ጠቅላላ ጉባኤ እኩል መብት ያላቸው ሆኖ የሚከተለው ኃላፊነትና ግዴታ ይኖራቸዋል፡-

ሀ. በኢ.አ.ፌ. የሚወጡትን በጠቅላላ ጉባኤ የሚፀድቁ ህግና ደንቦችን እንዲሁም ውሳኔዎችን የማክበርና የማስከበር፣

ለ. መተዳደሪያ ደንባቸውንና ልዩ ልዩ ደንብና መመሪያዎቻቸውን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ደንብና መመሪያን መሠረት በማድረግ የማዘጋጀት፣

ሐ. የኢ.አ.ፌ. በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች የመሳተፍ፣

መ. አጠቃላይ የየክልሉን የአትሌቲክስ ስፖርት እንቅስቃሴ የማሳወቅ፤

7. ማንኛውም የክልል/የከተማ አስተዳደር ፌዴሬሽን ከኢ.አ.ፌ. አባልነት የሚቋረጠው፡-

ሀ. የክልሉ/ የከተማው አስተዳደር ፌዴሬሽን ሲፈርስ፣

ለ. ያሉት ክለቦች እየፈረሱ ከ5 በታች ሲቀሩ ወይም

ሐ. ማሟላት ያለበትን ቅድመ ሁኔታ መጓደሉ ሲረጋገጥና በጠቅላላ ጉባኤ

## ክፍል ሦስት
## የኢ.አ.ፌ. አቋምና አደረጃጀት
## አንቀፅ ስምንት
## የፌዴሬሽኑ አቋም

1. የኢ.አ.ፌ. አደረጃጀትና አቋም፡-

ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ

ለ. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

ሐ. አግባብነት ያላቸው ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችና ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

2. ፌዴሬሽኑ የራሱ የሆነ የተሟላ ፅ/ቤት ይኖረዋል፡፡

## አንቀፅ ዘጠኝ
## ጠቅላላ ጉባኤ

የኢ.አ.ፌ. ጠቅላላ ጉባኤ የፌዴሬሽኑ የበላይ አካል ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የክልል አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንቶች ወይም ተወካዮች /በድምፅ/
2. የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንትና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት /በድምፅ/
3. የአትሌቶች ተወካዩች (በሁለቱም ፆታ) /በድምፅ/
4. የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽንን የሚወክል አንድ ተወካይ /ያለ ድምፅ/
5. በክልል ስፖርትን የሚመራው ተቋም አንድ ኃላፊ /ያለ ድምፅ/
6. የክልል አትሌቲክስ ፌደሬሽኖች በባለቤትነት ከሚያወዳድሯቸው ክለቦች አንድ ተወካይ /ያለ ድምፅ/
7. በጠቅላላ ጉባኤ የተሰየመ ኦዲተር /ያለ ድምፅ/
8. የዳኞችና የአሰልጣኞች አንድ አንድ ተወካይ /ያለ ድምፅ/
9. በጠቅላላ ጉባኤ የተሰየሙ የክብር አባላት /ያለ ድምፅ/
10. አግባብነት ያላቸው የፅ/ቤት ኃላፊዎች /ያለ ድምፅ/

## አንቀጽ አስር
## የጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

1. የሀገሪቱ የአትሌቲክስ ስፖርት የበላይ አካል ነው፡፡
2. የአትሌቲክስ ስፖርት እቅድና በጀት መርምሮ ያፀድቃል፣ ለተግባራዊነቱ መመሪያ ይሰጣል፡፡

3. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ስፖርት ኮሚሽን፣ በአህጉራዊና አለም አቀፍ የአትሌቲክስ ፌደሬሽኖች የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፣ የማሻሻያ ሃሣብ ያቀርባል፡፡
4. የፌዴሬሽኑን ደንቦችና መመሪያዎች ያፀድቃል፣ ተግባራዊ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፡፡
5. ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ፣ የፋይናንስና የኦዲት ሪፖርት ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ አመራር ይሰጣል፡፡
6. በፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተወሰኑ ከፍተኛ ቅጣቶችንና እገዳዎችን በመመርመር እንደአስፈላጊነቱ ምህረት ይሰጣል፡፡
7. አዲስ አባላትን ይቀበላል፣ የክብር አባላቱን ይሰይማል፡፡
8. የፌዴሬሽኑን የውጪ ኦዲተር ይሰይማል፡፡

## አንቀጽ አስራ አንድ
## ስብሰባና ምልዐተ ጉባኤ

1. ጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባውን በዓመት አንድ ጊዜ በመስከረም ወር ያካሂዳል፡፡ የተለየ ጉዳይ ካጋጠመ እስከ ሁለት ወር ድረስ ብቻ ሊያራዝም ይችላል፡፡
2. ከጠቅላላው ጉባኤ 2/3ኛው ሲስማሙ ልዩ ጠቅላላ ጉባኤው ሊጠራ ይችላል፣
3. ጠቅላላ ጉባኤው ከመካሄዱ 15 ቀናት በፊት የጉባኤውን አጀንዳ እና ሰነድ በፌዴሬሽኑ ፅ/ቤት አማካይነት መላክ ይኖርበታል፡፡
4. ድምፅ ያላቸው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት አጀንዳ እንዲያዝላቸው ከፈለጉ ከ1 ወር በፊት ለፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት በፅሁፍ ማቅረብ አለባቸው፣
5. የጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳ፣ ያለፈው ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ፣ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርትና የፋይናንስ ሪፖርት ጠቅላላ ጉባኤ ከመጠራቱ በፊት ለአባላት ይላካል፣
6. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ ቢያንስ በአንድ ወር አንድ ጊዜ ይካሄዳል፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፣
7. በማናቸውም የፌዴሬሽኑ ጠቅላላ ጉባኤ፣ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የንዑሣን ኮሚቴዎች ስብሰባ ከግማሽ በላይ አባላት ሲገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፡፡ ሁለት ጊዜ ስብሰባ ተጠርቶ አባላቱ ባይሟሉ በሦስተኛው ስብሰባ ላይ በተገኙ አባላቶች ስብሰባው ይከናወናል፣
8. መተዳደሪያ ደንቡን ለማሻሻል፣ እንዲሁም የፌዴሬሽኑን ህልውና ሊታደጉ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ውሣኔን የሚጠይቅ ጉባኤ ሲኖር የጠቅላላ ጉባኤው 2/3ኛው አባላት መገኘት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ አስራ ሁለት
## የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጥንቅርና የሥራ ዘመን

1. የፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የሚከተለው ጥንቅር ይኖረዋል፡፡
   ሀ. ፕሬዚዳንት
   ለ. ም/ፕሬዚዳንት
   ሐ. ዓቃቤ ነዋይ
   መ. አራት አባላት
   ሠ. ሁለት የአትሌት ተወካዮች /በድምፅ/
   ረ. የጽ/ቤቱ አስፈላጊ የስራ ኃላፊዎች በአስረጅነት /ያለ ድምፅ/

2. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሥራ ዘመን “4” ዓመት ይሆናል፡፡

3. ማንኛውም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ከኃላፊነቱ ሊነሳ የሚችለው በፌዴሬሽኑ ደንብና መመሪያ ብቻ ነው፡፡

4. አንድ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል መመረጥ የሚችለው በአንድ የስፖርት ፌዴሬሽን ብቻ ነው፡፡

5. አንድ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ውጤታማነቱ እና ፈቃደኝነቱ ካለ በተደጋጋሚ ሊመረጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሦስት
## የኘሬዚዳንት እና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እጩ ስለማቅረብ

1. እያንዳንዱ ክልልና የከተማ አስተዳደር ለኘሬዚዳንትነት እና ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት አንድ አንድ እጩ የማቅረብ መብት አለው፡፡

2. የክልል ፌዴሬሽኖች የሚያቀርቧቸውን ዕጩዎች በፌዴሬሽኑ ማህተም ተደርጎበት መቅረብ አለበት፡፡

3. የአትሌት ተወካዮች ከሁለቱም ፆታዎች አንድ አንድ ሰው በፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አማካይነት በአትሌቶች ይመረጣሉ፡፡

4. ዕጩዎች በኘሬዚዳንትነትና በሥራ አስፈፃሚነት ለመሥራት ፈቃደኝነታቸውን በፅሁፍ ያረጋግጣሉ፡፡

## አንቀጽ አስራ አራት
## የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት መምረጫ መመዘኛዎች

1. ኢትዮጵያዊ የሆነ፣
2. ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ፣
3. አትሌቲክስ ስፖርትን ለማገልገል ፈቃደኛ የሆነ፣
4. የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገ፣
5. መልካም ሥነ-ምግባር ያለው፣
6. በሕግ መብቱ ያልተገደበ፣
7. የአእምሮ ህመምተኛ ያልሆነ፣
8. ለአትሌቲክስ ስፖርት ዝንባሌና ፍቅር ያለው፣
9. ከክልሉ ዕጩ ሆኖ እንዲቀርብ በክልል ፌዴሬሽኑ ድጋፍ ያለው፡፡

## አንቀጽ አስራ አምስት
## የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

1. ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 የተጠቀሱትን ሁሉ ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. የጠቅላላ ጉባኤው ውሣኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ይፈፅማል፣
3. የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ እንዲያፀድቅለት ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፡፡ ሲፀድቅለት ተግባራዊ ያደርጋል፤
4. ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴና የፋይናንስ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፤
5. አስፈላጊ የሆኑ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ተግባራቸውንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የሥራ ጊዜያቸውንም ይወስናል፤
6. የውስጥ ደንቦችንና ልዩ ልዩ የሥራ መመሪያዎችን አዘጋጅቶ በሥራ ላይ ያውላል፤
7. ለፌዴሬሽኑ አስተዳደርና አመራር ውድቀት በግልና በጋራ ተጠያቂ ይሆናሉ፤
8. ከሥራ አስፈፃሚ አባልነት በገዛ ፍቃዳቸውም ሆነ በሌላ ምክንያት በሚሰናበቱ አባላት ምትክ በተጠባባቂነት ከተመረጡት ሁለት አባላት ውስጥ ቅድሚያ ያለውን የጠቅላላ ጉባኤን ሳይጠብቅ መተካት ይችላል፡፡ ጠቅላላ ጉባኤም አቅርቦ ያስፀድቃል፤
9. ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ስፖርት ኮሚሽን መ/ቤቱ ጋር በመተባበር ሥራውን ያከናውናል፤
10. የፌደሬሽኑን ሠራተኞች በመዋቅሩ መሠረት ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፤
11. ፌዴሬሽኑን የፋይናንስና ንብረት እንቅስቃሴ በሕጋዊ ኦዲተር በማስመርመር ለጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት እንዲቀርብ ያደርጋል፤
12. አገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ውድድሮችን ያዘጋጃል፣ ያሳትፋል፤
13. ዓመታዊ ዕቅድና በጀት እንዲሁም የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለስፖርት ኮሚሽንና የሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፡፡
14. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሥልጣኑን በከፊል ለጽ/ቤቱ አመራር ሊያስተላለፍ ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ ስድስት
## የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

1. በማንኛውም ሥፍራ ለፌዴሬሽኑ ሕጋዊ ተጠሪ ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
2. የፌዴሬሽኑን ገንዘብ ከጽ/ቤት ኃላፊው፣ ከፋይናንስ ኃላፊው ወይም ዓቃቤ-ንዋይ ጋር በመሆን ያንቀሳቅሳል፤
3. የጠቅላላ ጉባኤውንና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴን ስብሰባዎች ይመራል፣ ድምፅ እኩል ሲሆን ወሣኝ ድምፅ ይኖረዋል፤
4. የጠቅላላ ጉባኤና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሣኔዎች በትክክል መከናወናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
5. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተሟልቶ በማይገኝበት ጊዜና ኢመርጀንሲ ኮሚቴ የማይገኝ ሲሆን፤ ከማንኛውም ሁለት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ጋር ሆኖ ውሳኔ ሰጥቶ ጉዳዩን በሚቀጥለው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሰባት
## የም/ፕሬዘዳንቱ ሥልጣንና ተግባር

1. ፕሬዚዳንቱ በማይገኝበት ጊዜ ሁሉ ተግባራት እርሱን ተክቶ ይሠራል፤
2. የፕሬዚዳንቱ የቅርብ ረዳት ሆኖ አስፈላጊውን ሁሉ ይፈፅማል፤
3. ፕሬዚዳንቱና ም/ፕሬዘዳንቱ በሌሉበት ጊዜ ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መካከል የሚወከል አባል የዕለቱን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ይመራል፤

## አንቀጽ አስራ ስምንት
## የዓቃቤ-ነዋይ ሥልጣንና ተግባር

1. ፌዴሬሽኑ ፋይናንስ በደንቡ መሠረት ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
2. የፌዴሬሽኑ ንብረት በአግባቡ ገቢና ወጪ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
3. ለጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርበውን የፌዴሬሽኑን በጀት ይገመግማል፣ የማሻሻያ ሀሣብ ያቀርባል፤
4. ለጠቅላላ ጉባኤ አጠቃላይ የፋይናንስ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
5. ከፕሬዚዳንቱ፣ ከፅ/ቤቱ ኃላፊና ከፋይናንስ ኃላፊ ጋር በመሆን የፌዴሬሽኑን ገንዘብ ያንቀሳቅሳል፡፡

## አንቀጽ አስራ ዘጠኝ
## ስለ ኢመርጀንሲ ኮሚቴ

1. ኢመርጀንሲ ኮሚቴ ሆነው የሚሰየሙት የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት፣ ም/ፕሬዚዳንት እና አቃቤ ነዋይ ናቸው፡፡
2. ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ጊዜና አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ም/ፕሬዚዳንቱ ከአቃቤ ነዋይና አንድ አባል ጋር ውሳኔ ሰጥቶ ጉዳዩን በሚቀጥለው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ አቅርቦ ያስፀድቃል፡፡

## አንቀጽ ሃያ
## የኢመርጀንሲ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ውሳኔዎችን የሚፈልጉ ተግባራት ሲኖሩና ነገር ግን የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላት ተሟልተው በማይገኙበት ወቅት የስራ አስኪያጅ ኮሚቴውን ቦታ በመተካት አስፈላጊ የሆኑ ውሳኔዎችን ይወስናሉ፡፡
2. ውሳኔውን በሚወስኑበትና እንዲፈፅሙ በሚያዙበት ወቅት የተቀመጡትን ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት አለበት፡፡
3. ኮሚቴው ባከናወናቸው ተግባራት በሙሉ ተጠያቂነትና ኃላፊነት አለበት፡፡
4. በኮሚቴው የተከናወኑ ማናቸውም ተግባራት ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ቀርበው ማፀደቅ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ ሃያ አንድ
## ስለ ክብር አባልነት

1. የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቅራቢነት በዕድሜ ልክ የክብር አባልነት ሊሰይም ይችላል፡፡

2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውም በሚከተለው መስፈርት አማካኝነት ይመርጣል፡፡
   - ሀ. የኢትዮጵያ አትሌትክስ ስፖርት ለማስፋፋትና ለማሳደግ በተለያየ መልኩ በገንዘብ፣ በማቴሪያል፣ በቁሣቁስና በዕውቀት ከፍተኛ እርዳታ ያደረገ ግለሰብ ወይም ተቋም
   - ለ. ሀገርን ወክለው ከ20 ዓመት በላይ በውጤታማነት የቆዩ እና በኦሎምፒክ ውድድሮች ወርቅ ያስገኙ አትሌቶች፤
   - ሐ. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት ለሁለት ተርም ተመርጦ ያገለገለና በስራው ምስጉን ሆኖ በጠቅላላ ጉባኤ በክብር የተሠናበተ፤

3. ከላይ በተዘረዘሩት መመዘኛ መስፈርቶች መሠረት በጠቅላላ ጉባኤ የክብር አባል ሆኖ የተመረጠ ሰው፡ -
   - ሀ. የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሚያዘጋጃቸው ማናቸውም ሀገር አቀፍ ውድድሮች በክብር አባልነት በመገኘት ሽልማት ይሰጣል፡፡
   - ለ. በጠቅላላ ጉባኤ ላይ ያለ ድምፅ ይሳተፋል
   - ሐ. ለአትሌቲክስ ስፖርት መስፋፋትና ማደግ በሚዋቀሩ የተለያዩ ኮሚቴዎች አባል በመሆን ይሠራል
   - መ. የብሔራዊ ፌዴሬሽኑን ያማክራል
4. በክብር አባልነት የተመረጠ ሰው፡ -
   - ሀ. ሚስጥር ጠባቂ መሆን፤
   - ለ. የአትሌቲክስ ስፖርት ዕድገትን ከሚጐዱ ማናቸውም ተግባራት ላይ መቆጠብ፤
   - ሐ. የብሔራዊ ፌዴሬሽኑን ደንብና መመሪያ የማክበርና የማስከበር፤
   - መ. አትሌቲክስ ስፖርት እንዲስፋፋና እንዲያድግ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ የበኩሉን ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ጉዳዮች
## አንቀጽ ሃያ ሁለት
## ስለ የአትሌት ማናጀሮች

1. ፌዴሬሽኑ ለአትሌቶች ቴክኒካዊ ድጋፍ የሚያደርጉ የአትሌት ወኪሎች ጋር ተባብሮ ይሠራል፤
2. ለአትሌት ወኪሎች ፈቃድ የመስጠት ስልጣን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ነው፤
3. ማንኛውም የአትሌት ማናጀር ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፈቃድ ውጪ መሥራት አይችልም፤
4. የአትሌት ማናጀር በአለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሕገ-ደንብ መሠረት ከሚይዛቸው አትሌቶች ጋር ውል ካልፈፀመ በስተቀር ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፈቃድ አይሰጠውም፤
5. በአትሌቱና ማናጀሩ መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በአለም አቀፍ ፌዴሬሽኑ ደንብና በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ደንብ መሠረት ውሣኔ ይሰጣል፤
6. የፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጨማሪ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሦስት
## የፌዴሬሽኑ የገቢ ምንጭ

1. ከመንግስት የሚሰጥ ድጋፍ
2. ከውድድሮች የሚገኝ ገቢ
3. ከስፖርት ማዘውተሪያና ከመዝናኛ ገቢ
4. ከንብረት ሽያጭና ከኪራይ ገቢ
5. ከስጦታና ከእርዳታ የሚገኝ ገቢ

6. ከማስታወቂያና ከስፖንሰርሽፕ የሚገኝ ገቢ
7. ከዓመታዊ የአባልነት ክፍያ
8. ፌዴሬሽኑ ከሚያቋቁማቸው የገቢ ማስገኛ ተቋሞች ከሚገኝ ገቢ እና
9. ልዩ ልዩ ገቢዎች

## አንቀጽ ሃያ አራት
## የገቢ ማስገኛ ተቋም ስለማቋቋም

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የአትሌቲክስ ስፖርቱን ለማሳደግና ለማስፋፋት ያግዘው ዘንድ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመነጋገር በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ መሰማራት እና ልዩ ልዩ ተቋማትን ሊያቋቁም ይችላል፣ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አምስት
## የፋይናንስ እንቅስቃሴ

1. ፌዴሬሽኑ የራሱ የባንክ አካውንት ይኖረዋል፤
2. ማንኛውም ወጪ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይወሰናል፣ ሆኖም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በከፊል ለጽ/ቤቱ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚያፀድቃቸው ወጪዎች መሠረት የፌዴሬሽኑ ገንዘብ በፌዴሬሽኑ ፕሬዘዳንት፣ በጽ/ቤት ኃላፊውና በአቃቤ ነዋይ ወይም በፋይናንስ ኃላፊው ፊርማ ይንቀሳቀሳል፡፡ ሆኖም ፕሬዘዳንቱ ከሌለ ም/ፕሬዘዳንቱ እርሱን ተክቶ ሊፈርም ይችላል፤
4. ለፌዴሬሽኑ እንቅስቃሴ ከመንግስት የሚሰጠው የበጀት ድጋፍና ድጎማ እንዲሁም ማናቸውም ገቢዎች በፌዴሬሽኑ የባንክ ሂሣብ ገቢ ይሆናል፤
5. ለጥቃቅን ወጪዎች የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተወስኖ በገንዘብ ያዥ እጅ ይቀመጣል፤
6. የፌዴሬሽኑ የግዥ፣ የፋይናንስ፣ የንብረትና የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክተር በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተወሰነውን ፒቲ ካሽ በፌዴሬሽኑ በወጣው የፋይናንስ መመሪያ መሠረት ያንቀሳቅሳል፤
7. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የፌዴሬሽኑን ገንዘብ አሰባሰብና አወጣጥ በአብዛኛው ቅድሚያ ሊሰጣቸው ለሚገባ የልማት እቅዶች እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤
8. የፌዴሬሽኑ የግዥ፣ የፋይናንስ፣ የንብረትና የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክተር በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተዘጋጅቶ በጠቅላላ ጉባኤ ከፀደቀ በኂላ ተፈፃሚ ይሆናል፤

## አንቀጽ ሃያ ስድስት
## ስለግጭት አፈታት

1. በአትሌቶችና በአትሌት ማናጀሮች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በአለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ደንብ ቁጥር 60 መሠረት ይፈታሉ፤
2. በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንና በአለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በአይ.ኤ.ኤ.ኤፍ ደንብ ቁጥር 60 መሠረት ይፈታል፤
3. በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንና በሌሎች አለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አባል ሀገራት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በአይ.ኤ.ኤ.ኤፍ. ደንብ ቁጥር 60 መሠረት ይፈታል፤
4. በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በክልል ፌዴሬሽኖች፣ በክለቦች፣ በዳኞች፣ በአትሌቶች አሰልጣኞች፣ በባለሙያዎችና በሠራተኞች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በፌዴሬሽኑ ልዩ ልዩ መመሪያዎች እና በአለም አቀፍ ደንብ መሠረት የሚፈቱ ይሆናል፤

## አንቀጽ ሃያ ሰባት
## የተከለከለ ተግባር

1. ማንኛውም የአትሌቲክስ ስፖርት ማህበራት በሀይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በጎሣና በዘር መደራጀት አይችሉም፤
2. አንድ ሰው በሥራ አስፈፃሚ ወይም በቋሚ ኮሚቴ አባልነት ሊያገለግል የሚችለው በአንድ የስፖርት አይነትና በአንድ ክለብ፣ ክልል ወይም ሀገር አቀፍ ፌዴሬሽን ብቻ ነው፡፡
3. የብሔራዊ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ ያፀደቃቸው የተከለከሉ ተግባራት መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡

## አንቀጽ ሃያ ስምንት
## ስለመፍረስ

1. የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሊፈርስ የሚችለው በጠቅላላ ጉባኤ 2/3ኛው ድምፅ ሲወሰን ነው፤
2. ፌደሬሽኑ በፈረሰ ጊዜ የፌዴሬሽኑ ሀብት የአትሌቲክስ ስፖርት ሊያስፋፋ ለሚችል አካል በጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔ መሠረት ይሰጣል፤
3. የፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ወይም አባላት ኃላፊነታቸውን በብቃት መወጣት ሳይችሉ ሲቀር በራሱ ውሳኔ ወይም በጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔ ብቻ ከኃላፊነቱ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ
## ቅጣት

ይህንን ደንብ የጣሰ ወይም የዚህን ደንብ አፈፃፀም ያሰናከለ ማንኛውም አካል አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይቀጣል ፌዴሬሽኑም የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሠላሣ
## ይህን ደንብ ስለ መተርጎም

በዚህ ደንብ ላይ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ደንቡን የመተርጎም ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ ሠላሣ አንድ
## ስለማሻሻል

ይህ ደንብ በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ጥያቄ ወይም በጠቅላላ ጉባኤ አባላት 2/3^ኛው^ እንዲሻሻል ሲጠይቁ ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሠላሣ ሁለት
## ስለ ሥራ ቋንቋ

የፌዴሬሽኑ የሥራ ቋንቋ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መንግስት የስራ ቋንቋ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ሠላሣ ሦስት
## መመሪያ ስለማውጣት

የብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በዚህ ደንብ መሠረት ልዩ ልዩ መመሪያዎችንና ደንቦችን የማውጣት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ ሠላሣ አራት
## ጽ/ቤቱ የሚገኝበት ቦታ

ጽ/ቤቱ በፌዴራል መንግስቱ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ሠላሣ አምስት
## ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በጠቅላላ ጉባኤ ከፀደቀበት ከህዳር 25 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ብስራት ጋሻውጠና
የኢ.አ.ፌ. ኘሬዚዳንት

# የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን
# የክለቦች ማቋቋሚያ መመሪያ

ህዳር 2003
አዲስ አበባ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በአዲስ መልክ ሥራዎችን ለመስራት ብሎም የአትሌቲክስን ስፖርት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስና ሀገራችን በአለም አቀፍ መድረክ፣ በአትሌቲክሱ መስክ ያላት ተወዳዳሪነት ለማሣደግ ባለው ፅኑ ፍላጐት መሠረት ይህንኑ ራዕይና ዕሣቤ ሊያሳኩ የሚችሉ ልዩ ልዩ መመሪያዎችና አሠራሮችን በመዘርጋት ላይ ይገኛል፡፡

እነሆ ለዚህም ያግዘው ዘንድ የክለቦች አደረጃጀትን በመፈተሽ ክለቦች ከተደጓሚነት ወጥተው ራሳቸውን የሚችሉበት ሁኔታ ለማመቻቸት ደመወዝ፣ ትጥቅ ህክምና ወዘተ… በርካታ ወጪ አውጥተው በሚያበቋቸው አትሌቶች ቢያንስ በትንሹ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማሰብ፤ በአጠቃላይ የአትሌቲክሱን ስፖርት ወይም በዚህ ዙሪያ የሚሠሩ የስፖርት ማህበራትን ወደ አትራፊነት (ወደ ቢዝነስ አስተሳሰብ) ለመቀየር ይህ የክለቦች ማቋቋሚ መመሪያ ወጥቷል፡፡

### የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን
### የክለቦች ማቋቋሚያ መመሪያ

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ
### አንቀጽ አንድ
### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የክለቦች ማቋቋሚያ መመሪያ ቁጥር ……………. ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ ሁለት
### አውጭው አካል

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ስፖርት ኮሚሽን የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን ባወጣው መመሪያና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይህ የክለቦች ማቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ ወጥቷል፡፡

## አንቀጽ ሦስት
## የመመሪያው አላማና አስፈላጊነት

የአገራችን የአትሌቲክስ ስፖርት እንዲጠናከርና ምርጥ አትሌቶችን ለማፍራት ታዳጊ፣ ወጣትና አዋቂ አትሌቶችን በመያዝ ወቅታዊና ሳይንሳዊ ስልጠና በመስጠት ክለባቸውንና አገራቸውን የሚያስጠሩ ምርጥ አትሌቶች ማፍራት፡፡

## አንቀጽ አራት
## ትርጓሜ

1. የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ማለት፡- የአትሌቲክስ ስፖርትን በመላ ሀገሪቱ ለማስፋፋትና ለመምራት በህግ ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፡፡
2. የአለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን (IAAF) ማለት፡ - የአትሌቲክስ ስፖርት በአለም አቀፍ ደረጃ በበላይነት የሚመራ አካልነው፡፡
3. ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ማለት፡ - በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር ውስጥ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋትና ለመምራት በህግ ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፡፡
4. የአትሌቲክስ ስፖርት ማለት፡ - የመም፣ የሜዳ ተግባር፣ የጐዳና ላይ ሩጫ፣ የርምጃ፣ የአገር አቋራጭና የተራራ ላይ ሩጫ ማለት ነው፡፡
5. ክለብ ማለት፡ - የአትሌቲክስ ስፖርት እንቅስቃሴን ለማራመድ የተቋቋመ ማህበር ነው፡፡
6. አትሌት ማለት፡ - በአትሌቲክስ ስፖርት የሚሳተፍ ሰው ነው፡፡
7. አገር አቀፍ ውድድር ማለት፡ - ከአንድ ክልል በላይ የሚሳተፉበት የአትሌቲክስ ውድድር ነው፡፡
8. ኢንተርናሽናል ውድድር ማለት፡ - ከአንድ አገር በላይ የሚሳተፉበት የአትሌቲክስ ውድድር ነው፡፡
9. የአትሌት ወኪል ማለት፡ - በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፈቃድ የተሰጠውና ከአትሌቶች ጋር በሚኖረው ስምምነት መሠረት የስልጠናና የአለም አቀፍ ውድድሮች ድጋፍ የሚያደርግ ወኪል ነው፡፡
10. አሠልጣኝ ማለት፡ - በአንድ ሕጋዊነት ባለው ክለብ ተገቢውን የቅድሚያ ሁኔታ በማሟላት በክለቡ ተቀጥሮ ለአትሌቶቹ ተገቢውን ሙያዊ ሥልጠና የሚሰጥ ማለት ነው፡፡
11. ታዳጊ አትሌት ማለት፡ - ዕድሜው ከ15 እስከ 17 ዓመት ያለ አትሌት ማለት ነው፡፡
12. ወጣት አትሌት ማለት፡ - ዕድሜው ከ18-19 ዓመት ያለ አትሌት ማለት ነው፡፡
13. አዋቂ አትሌት ማለት፡ - ዕድሜው 20 ዓመት እና ከ20 ዓመት በላይ የሆነ አትሌት ማለት ነው፡፡

# ክፍል ሁለት
## ስለክለቦች አመሠራረት፣ አቋምና ምዝገባ
## አንቀጽ አምስት
## ክለብን ስለመመስረት

1.የአትሌቲክስ ክለቦች በመኖሪያ አካባቢና ከተሞች፣ በድርጅቶች፣ ፋብሪካዎች እና በትምህርት ተቋማት ስፖርቱን ለንግድ (ለትርፋማነት) በሚጠቀሙ ባለሀብቶች ሊመሠረቱ ይችላሉ፡፡

2.ማንኛውም የሚቋቋም ክለብ፡ -

ሀ. የማቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ፣

ለ. መጠሪያ ስምና አርማ፣

ሐ. ጽ/ቤትና የክለብ ስራ አስኪያጅ፣

መ.ቢቻል የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ፣ በባለቤትነት ወይም በኪራይ ወይም በትውስት ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሠ. በሀገር አቀፍ ፌዴሬሽን የተረጋገጠ ህጋዊ የሆነ የአሠልጣኝነት ማስረጃ ያላቸው ቢያንስ አንድ ባለሙያ፣

ረ. ህጋዊ በሆነ መልኩ የተመዘገቡና መዋጮ የሚደረጉ ደጋፊዎች ያሏቸው፣

ሰ. በስሙ የባንክ ሂሳብ መክፈት የሚችል፣

ሸ.የያዛቸውን አትሌቶች በሁለቱም ፆታ ቢያንስ 25 ሆነው ቢያንስ በሁለት የውድድር ዓይነቶች ማለትም፤ በውርወራ፣ በዝላይ ወይም በሩጫ ተወዳዳሪ አትሌቶች ያላቸው፣

ቀ. የአገር አቀፍ ፌዴሬሽኑንና የክልል ፌዴሬሽኑን መተዳደሪያ ደንቦችና የሚያስተላልፏቸውን ውሳኔዎች የሚቀበል ስለመሆኑ በጽሁፍ ማረጋገጥ የሚችል፣

በ. የፅ/ቤት ቋሚ አድራሻ፡ - (ወረዳ፣ የቤት ቁጥር፣ ስልክ ቁጥርና ኢሜል የመሳሰሉት ያለው)

ተ. ክለቡ የሚይዛቸው አትሌቶች ስርጭት ቢያንስ በሃደት በታዳጊ፣ በወጣትና በአዋቂ ለማዋቀር የተዘጋጀ፣

## አንቀጽ ስድስት
## የክለቦች አቋም

የአትሌቲክስ ስፖርት ክለቦች አቋም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

1. ጠቅላላ ጉባኤ
2. ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
3. ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችና ንዑሳን ኮሚቴዎች
4. የክለብ ፅ/ቤት ኃላፊ፣ አሠልጣኞች፣ አትሌቶች እና ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## <u>አንቀጽ ሰባት</u>
## <u>ስለ ክለቦች ምዝገባ</u>

1. ክለቦች በአንቀጽ 4 ቁጥር 2 የቅድሚያ መቋቋሚያ መስፈርቶችን አሟልተው ሲገኙ በሚከተለው አኳኋን ክለባቸውን በማቋቋም ይመዘገባሉ፡፡
2. የመቋቋሚያ መመዘኛዎችን የሚያሟሉ ክለቦች በተቋቋሙበት፣ ክልል በሚገኘው የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን የምዝገባ ጥያቄ ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም 30 ድረስ በፅሁፍ ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. ጥያቄው የቀረበለት የክልል አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ክለቡ ያቀረበውን መመዘኛዎች ማሟላቱን ካረጋገጠ በኂላ ይመዘግባል፣
4. የክልል ፌዴሬሽኑ ክለቡ መመዘገቡን የሚገልጽና ክለቡ ክልሉ በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች መሳተፍ የሚችል መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ ለክለቡና ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ያሳውቃል፡፡
5. ክለቡ ክልሉ በሚያዘጋጀው ውድድር ለአንድ ዓመት ከቆየ በኂላ ያለውን የብቃት ደረጃ በማሳደግ በዓመቱ መጨረሻ ለብሔራዊ ፌዴሬሽኑ የምዝገባ ጥያቄ የክልሉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ማቅረብ ይችላል፡፡
6. የክልል ፌዴሬሽኑ በዓመት ውስጥ የክለቡን ዓመታዊ ክፍያ፣ የጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት፣ የተወዳዳሪ አትሌቶች ተሳትፎ፣ ስፖርቱን ለማሳደግ የያዛቸው ዕቅዶች፣ የውድድር ብቃትና ሌሎች ሁኔታዎችን የሚያሟላ መሆኑን ካረጋገጠ በኂላ ለብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ይልካል፡፡
7. ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ የቀረቡለትን መመዘኛዎች ከመረመረ በኂላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለክልል ፌዴሬሽኑ መልስ በመስጠት እውቅና ይሰጣል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>ስለ አትሌቶች ቅጥር፣ ተገቢነት፣ መብትና ግዴታ</u>
## <u>አንቀጽ ስምንት</u>
## <u>የአትሌት ምዝገባ ሂደት</u>

1. ማንኛውም ክለብ በራሱ መመዘኛ የፈለገውን አትሌት መመልመልና መቅጠር ይችላል፡፡
2. አንድ አትሌት በአንድ የውድድር ዘመን ተገቢነት የሚያገኘው በፍቃደኝነት ለፈረመበት/ችበት ክለብ ብቻ ነው፡፡
3. አንድ አትሌት ከአንድ ክለብ ጋር ስምምነት ካደረገ በኂላ ስምምነቱ በሶስት ኮፒ ተሰርቶ አንደኛው ለክልሉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሁለት እያንዳንዳቸው ለአትሌቱና ለክለቡ ከተሰጠ በኂላ ስምምነቱ በስራ ላይ ይውላል፡፡
4. በአትሌቱና/ቷና በክለቡ መካከል የሚደረገው የጋራ የውል ስምምነት ዘመን ከ_________ እስከ _________ በሚል በውል ስምምነት ፎርማ ይፈጸማል፡፡ የአትሌቱ ተገቢነት የሚፀድቀው በክልሉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ይሆናል፡፡
5. በአትሌቱና በክለቡ የተደረገውን ውል ሁለቱም አካሎች በጋራ በመስማማት ማፍረስ ይችላሉ፡፡ የዚህንም ጉዳይ የሁለቱ ተዋዋዩች ፊርማና የክለቡ ማህተም በማድረግ ለክልሉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ማሳወቅ አለባቸው፡፡
6. ሁለቱም ውል ተዋዋዩች በጋራ የተስማሙበትን ውል አንደኛው ወገን ፍላጐት ማፍረስ አይችልም፡፡ ሆኖም ግን አንደኛው ወገን በራሱ ጊዜ ውሉን ካፈረሰ ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች የተስማሙበት ውል እንደተጠበቀ ሆኖ ውል አፍራሹ ውል ለፈረሰበት ወገን ብር 15,000.00 (አስራ አምስት ሺህ ብር) ካሣ በመክፈል ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል፡፡
7. ሁለት ተዋዋዩች ውላቸውን ጨርሰው እንደገና ለማደስ ከፈለጉ የሁለቱን ተዋዋዩች ፊርማ በክለቡ ማህተም አስደግፎ ለክልሉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ማቅረብ ማሳደስ ይቻላል፡፡
8. አንድ ክለብ በገባው ውል መሠረት አትሌቱ/ቷ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ሲያጣና አትሌቱ/ቷ ሁኔታውን ለክልሉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ካሳወቀ ፌዴሬሽኑ ሁኔታውን ካጠና በኂላ በደንቡ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡
9. አንድ አትሌት በአንድ የውድድር ዘመን ለሁለት ክለቦች ፈርሞ ተገቢነት ተሰጥቶት ሲወዳደር ቢገኝ አትሌቱ/ቷ ብር 5,000.00 (አምስት ሺህ ብር) የሚቀጣ ሲሆን፤ ተገቢነቱ ቀድሞ ለፈረመበት ክለብ ይሆናል፡፡ በተከሰሰበት ውድድር ያስመዘገበው ውጤትም ይሰረዛል፡፡
10. አንድ አትሌት ከነበረበት/ችበት ክለብ ጋር በዘመኑ የገባው ውል ፈጽሞ በነበረበት ክልል በሚገኝ ክለብ ለመመዝገብ ከፈለገ ከነበረበት ክለብ በሚሰጠው መልቀቂያ ሊመዘገብ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል የሚዘዋወር ከሆነ የክልሉን አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መልቀቂያ መያዝ አለበት፡፡
11. የአትሌቶችን የዝውውር ሂደት የሚፈቅደውና የሚያጸድቀው የክልሉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ነው፡፡
12. የአትሌቶችን ተገቢነትና ዝውውር ጉዳይ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በይግባኝ የማየትና የመወሰን ሙሉ ስልጣን አለው፡፡

## <u>አንቀጽ ዘጠኝ</u>
## <u>የአትሌት ኃላፊነትና ግዴታ</u>

በአንድ ክለብ ተይዞ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ አትሌት ለክለቡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መፈፀም አለበት፡፡

1. በውድድር የመሣተፍ፣
2. ማንኛውም አትሌት በብሔራዊ ፌዴሬሽኑ አገርን ወክለው የሚካሄዱ አለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ተሳትፎ በቡድን ከሚያገኙት ሽልማት 10% ለብሔራዊ ፌዴሬሽኑ መክፈል አለበት፡፡
3. በአትሌቱና በክልሉ/በክለቡ በሚፈፀም ውል መሠረት አትሌቱ ወደሌላ ክልል/ክለብ ሲዛወር የሚፈለግበትን ክፍያ በአንቀፅ 8 ቁጥር 6 በተገለፀው መሠረት መፈፀም ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ አስር
## አትሌቱ ማግኘት ስለሚገባው ጥቅም

1. አትሌቱ በክለቡ የሚያገኘው ጥቅማጥቅም በክለቡና በአትሌቱ በሚያደርጉት ውል መሠረት ሆኖ ቢያንስ፡ -
   ሀ. ደሞዝ
   ለ. የስፖርት ትጥቅ
   ሐ. የትራንስፖርት አገልግሎት (አበል)
   መ. የተሟላ ስልጠና
   ሠ. ህክምና ሊያሟላ ይገባል
2. በክልል ወይም በማናጀር የታቀፈ አትሌት ከላይ በአንቀፅ 10 ቁጥር 1 የተገለፀው መብት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
## አንቀጽ አስራ አንድ
## ስለ ስም ለውጥ

አንድ ክለብ በራሱ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት የክለቡን መጠሪያ ስም መለወጥ ይችላል፡፡ ይህንንም ውሳኔ ለክልሉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አሳውቆ ካፀደቀ በኋላ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ሆኖም ግን የሌላ በስራ ላይ ያለ ወይም ተቋቁሞ የፈረሰ የአትሌቲክስ ስፖርት ክለብ ስም ወይም ተመሳስሎ ሶስተኛ ወገን ሊያደናግር የሚችል ስም መጠቀም አይቻልም፡፡

## አንቀጽ አስራ ሁለት
## ስለ ውህደት

በአንድ ክልል በሚገኙ ሁለት ክለቦች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት ሊዋሀዱ ይችላሉ፡፡ መጠሪያቸውም ሁለቱም በተስማሙበት የሚወሰን ሲሆን ይህንንም ውሳኔ ለክልል አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አቅርበው በማፀደቅ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

## አንቀጽ አስራ ሦስት
## ስለመፍረስ

አንድ ክለብ በራሱ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት ሊፈርስ ይችላል፡፡ መፍረሱንም ለክልሉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ያሳውቃል፡፡ የክልሉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንም በ30 ቀናት ውስጥ ለብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ያሳውቃል፡፡

## አንቀጽ አስራ አራት
## ስለ ቅጣት

ማንኛውም ክለብ በክልልና በአገር አቀፍ ፌዴሬሽኑ የወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ጥሶ በተገኘ ጊዜ የክልል ፌዴሬሽኑ በሥነ-ምግባር ደንብ መመሪያ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤ የክልል ፌዴሬሽኑ የማስተካከያ እርምጃ ባልወሰደ ጊዜ ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ጉዳዩን አጣርቶ አስፈላጊውን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ አምስት
## መመሪያውን ስለመተርጐም

በዚህ መመሪያ ላይ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ጉዳዩች ሲያጋጥሙ የብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ የመተርጐም ስልጣን ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ አስራ ስድስት
## መመሪያውን ስለማሻሻል

በዚህ መመሪያ በሰፈሩት ጉዳይ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ አሻሚ ትርጉም የሚያስጡ ሁኔታዎች ቢያጋጥሙ የፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሰባት
## የመመሪያው ተፈፃሚነት

በክልል ፌዴሬሽን፣ በክለብ፣ በአትሌቶችና በአሠልጣኞች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አስራ ስምንት
## መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከፀደቀበት ከ ህዳር 25 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ብስራት ጋሻውጠና
የኢ.አት.ፌ. ፕሬዚዳንት

# የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አካላት የስነምግባር መመሪያ

ህዳር 2003
አዲስ አበባ

## መ ግ ቢ ያ

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የቆመለትን የአገሪቱን የአትሌቲክስ ስፖርት የማሳደግ ተልዕኮውን በላቀ ደረጃ ከግብ ለማድረስ በሚያደርገው ጥረት አሠልጣኞች፣ አትሌቶችና ክለቦች በስፖርታዊ እንቅስቃሴም ሆነ በማህበረሰባዊ ኑሮ ዙሪያ የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ ስፍራ እንዳላቸው በማመን ነው፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ዓላማዎች በአብዛኛው የሚያተኩሩ በተሳታፊዎች ገንቢ የሆነ የባህሪ ለውጥ በማስገኘት ላይ ስለሆነ ተሳታፊዎች የተስተካከለ ባህሪና የተሟላ ስብዕና ያላቸው ጠቃሚ ዜጐች እንዲሆኑ ያላሰለሰ ጥረት ሉደረግ ስለሚገባና ይህም የአትሌቲክስ ስፖርት ተሳታፊዎች እንቅስቃሴና የማህበራዊ አኗኗር ዘይቤ በደንብና በስርዓት አንዲመራ የሚያስገድድ በመሆኑ ነው፡፡

አሠልጣኞች፣ አትሌቶች የውድድር ዳኞችና ክለቦች ብሔራዊ ፌዴሬሽን የሚሰጠውን አገልግሎት ስርዓት ባለው መንገድ በመጠቀም የግልና የጋራ ዓላማዎችን ዕውን ለማድረግ አጋዥ እንደሚሆን በማመን ነው፡፡

ይህ የሥነ-ምግባር መመሪያ ደንብ የአትሌቲክስ ስፖርት ተሳታፊዎች በሚያደርጓቸው ተሳትፎ ዙሪያ ሊከሰቱ የሚችሉ የሥነ-ምግባር ጉድለቶችና በአንፃሩም እነኚህ ባህሪያት ሊስተካከሉ የሚችሉባቸውን የሥነ-ሥርዓት እርምጃዎችንና ውሳኔዎችን አካትቶ ቀርቧል፡፡

ይኸው መሠረታዊና ዓብይ አላማ ግቡን እንዲመታና ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት የሚቻለው ተሳታፊ አካላቱ ከፌዴሬሽኑ ጐን በመሆን የድርሻቸውን ሲወጡ መሆኑን ለማመን ይህ ደንብ ተግባራዊ እንዲሆን ተወስኗል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ
### አንቀጽ አንድ
### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አካላት የሥነ-ምግባር ቁጥር አንድ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ ሁለት
### አውጪው አካል

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በተሻሻለው መመሪያ መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### አንቀጽ ሦስት
### ትርጓሜ

1. “ክለብ” ማለት የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማሳደግ በክለብ ደረጃ ተመዝግበው የማወዳደሩበት የስፖርት ማህበር ነው፡፡

2. “አትሌት” ማለት በክለብ፣ በክልልና በማናጀር ደረጃ ተመዝግበው ክለባቸውን በመወከል በተለያዩ የተግባር ውድድሮች የሚሳተፍ/የምትሳተፍ ማለት ነው፡፡

3. “አሠልጣኝ” ማለት በአንድ ሕጋዊነት ባለው ክለብ፣ ክልልና ማናጀር ተገቢውን የቅድሚያ ሁኔታ በመከተል በክለቡ ተቀጥሮ ለአትሌቶች ተገቢውን ስልጠና የሚሰጥ/ምትሰጥ ማለት ነው፡፡

4. “ህጋዊ ማናጀር” ማለት የአትሌቶች ወኪል በመሆን ከአይ.ኤ.ኤ.ኤፍ እና ከኢትዮጵያ ብሔራዊ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ህጋዊ ዕውቅና ያለው አትሌቶችን በተለያዩ ውድድሮች ላይ እንዲሳተፉ የሚያደርግ/ምታደርግ ህጋዊ አካል ነው፡፡

5. “የክልል አትሌቲክስ ፌዴሬሽን” ማለት በብሔራዊ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን እውቅናና ፈቃድ ተሰጥቶት ባለበት ክልል የአትሌቲክስን ስፖርት ለማሳደግና ለማስፋፋተ በስሩ የተለያዩ የአትሌቲክስ ክለቦችን ኘሮጀክቶችን፣ አሠልጣኞችንና ባለሙያዎችን የያዘ የስፖርት ማህበር ነው፡፡

6. “አካላት” ማለት በኢትዮጵያ አትሌቲክስ እንቅስቃሴ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚሳተፉ ሆነው አማተር አገልጋዩች፣ አሠልጣኞች፣ አትሌቶች ክለቦች እና የክልል ፌዴሬሽኖችን ያጠቃልላል፡፡

### አንቀጽ አራት
### የመመሪያው አስፈላጊነትና አላማ

በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ አካላት ለሥነ-ሥርዓት ተገዥ እንዲሆኑ ለመርዳት ብሎም በሀገር አቀፍ ደረጃ ውጤት ለማስመዝገብ እንዲቻል ለማድረግና ከአሁን በፊት በተግባር ባለመዋሉ በስልጠና፣ በውድድርና በጉዞ ሂደት የፌዴሬሽኑን ደንብና ሥርዓት በመከተል አሠልጣኞችና አትሌቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ክፍተት ያለው በመሆኑ የስልጠናና የውድድር ሂደቶችን የሚያጓትቱ ጥፋቶችን ለመቀነስና ለስልጠናው ዘመናዊ ስልት እንዲከተል ባለመደረጉ ምክንያት ይህንኑ ለማስተካከል ይህን መመሪያ ማውጣት አስፈልጓል፡፡

### አንቀጽ አምስት
### የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በፌዴሬሽኑ አማተር አገልጋዩች በአሠልጣኞች በሚያቋቁማቸው በአሠልጣኞች፣ በክልል ፌዴሬሽኖች፣ ክለቦችና በአትሌቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ አትሌቶችና አሠልጣኞች ሥነ-ምግባር
### አንቀጽ ስድስት
### የአትሌቶችን መብት

1. የሚሰለጥኑበት በቂ ጊዜ ሊኖራቸው ይገባል፣
2. በውድድር ዝግጅት ወቅት በቂ ምግብና ዕረፍት ማግኘት አለባቸው፣
3. የስፖርት ትጥቆች፣ የመጠቀሚያ መሳሪያዎችና የማዘውተሪያ ቦታዎች የመጠቀም፣
4. በስልጠናና በውድድር ወቅት ለሚከሰቱ ስፖርታዊ ጉዳቶች አትሌቱ በብሔራዊ ቡድን የታቀፈ ከሆነ ከብሔራዊ ፌዴሬሽኑ አለበለዚያ ከክልሉ፣ ከክለቡ ወይም ከማናጀሩ ህክምና የማግኘት፣
5. በፌዴሬሽኑ የውሳኔ ሂደት በተወካዩቻቸው አማካኝነት በቋሚነት በሁለቱም ፆታ የመሳተፍ፣
6. በሚወዳደሩበት ተግባር በቂና ትክክለኛ ስልጠና የማግኘት፣
7. ከማንኛውም አድሎ የፀዳ አገልግሎት የማግኘት፣
8. ማንኛውም አትሌት ከሥነ አእምሮአዊ፣ አካላዊና ወሲባዊ ትንኮሳ ነፃ የመሆን መብት፣
9. የውድድሩ ዓይነት ጊዜ፣ ቦታ አስቀድሞ የማወቅ፣
10. በሀገር ውስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ውድድሮች ያገኛቸውን የገንዘብ ሆነ የቁሳቁስ ሽልማቶች በፌዴሬሽኑ በመመሪያ መሠረት የማግኘት፣
11. በማንኛውም መልኩ ለሚያጋጥሙ ችግሮች የፌዴሬሽኑን ደንብ በመከተል አቤቱታ የማቅረብ እና ተገቢውን ምላሽ የማግኘት፣

## አንቀጽ ሰባት
## የአትሌቶች ኃላፊነት

1. የግል ንፅህናውን፣ የልምምድና የውድድር ትጥቁን፣ የመጠቀሚያ መሳሪያዎችን የማዘውተሪያ ቦታዎችን በንፅህና፣ በጥንቃቄና በእንክብካቤ የመያዝ፣
2. በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ የሚያርፍባቸው ክፍሎችና አካባቢውን በንፅህና የመያዝ፣ በአግባቡ የመጠቀምና በመጨረሻም በትክክል የማስረከብ፣ የደረሰ ጥፋት ሲኖር ተጠያቂ የመሆን፣
3. በልምምድም ሆነ በውድድር ቦታ ከሌላው አትሌት ጋር መግባባትና መከባበር፣
4. በማንኛውም ቦታ ላይ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ሥነ አዕምሮአዊ፣ አካላዊ ይሁን ወሲባዊ ትንኮሳ መፈፀም ከሥነ-ምግባር ውጪ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በሕግም የሚያስጠይቅ መሆኑን ማወቅ፣ ይህን ተክትሎ ለሚመጣ በግል ጉዳይ ተጠያቂ የመሆን፣
5. ለጋራ ዓላማ ሲባል ከአሠልጣኝ ጋር ተግባብቶ፣ ተከባብሮ አብሮ የመስራት፣
6. ለልምምድ፣ ለውድድር፣ ለጉዞ ፎርማሊቲ ማሟላት ሆነ ለሽልማት ጉዳዮች በአሠልጣኙና በፌዴሬሽኑ በሚገለፅለት ቦታና ጊዜ አስፈላጊውን ዝግጅት በማሟላት ቀድሞ የመገኘት፣
7. ለአትሌቱ ዕድገትና ውጤታማነት ከሚሰሩ ማናቸውም ክፍሎች በውድድርና በልምምድ ቦታ በህክምና ወዘተ… ተመድበው ከሚሰሩ የፌዴሬሽኑ ሠራተኞችና ሌሎች አጋዥ አጋሮች ጋር ተግባብቶ የመስራት፣
8. ፌዴሬሽኑ የሚያወጣውን ደንብና መመሪያ እንዲሁም ትዕዛዝ የመቀበልና ተግባራዊ የማድረግ፣
9. ማንኛውም በብሔራዊ ቡድን የተመረጠ አትሌት ፌዴሬሽኑ በመደበለት አሠልጣኝ የመሰልጠን ቅሬታ ካለም በአግባቡ ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ፣
10. ያለ ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ዕውቅናና ፈቃድ የውጭ ኢንተርናሽናል ውድድር ያለማድረግ፣
11. ሀገርን ለሚወክሉ ውድድሮች ቅድሚያ የመስጠት፣ በሀገር ውስጥ ለሚደረጉ ውድድሮች ቅድሚያ መስጠትና መሳተፍ፣
12. በውድድር ወቅት የዳኞችን ውሳኔ የመቀበል ተቃውሞ ካለ ህጉ በሚያዘው መሠረት የማመልከት፣
13. ለውድድር አስተባባሪዎችንና ተመልካቾች ያልተገባ ፀባይ አለማሳየት፣
14. ማንኛውም በውሰት የወሰዳቸውን የፌዴሬሽኑን ንብረቶች በተገቢው ሰዓትና በተጠየቀበት ወቅት የመመለስ፣
15. ለፌዴሬሽኑና ለክለቡ ገቢ ሊያደርገው የሚገባውን የገንዘብ መጠን ወቅቱ ሳያልፍ ገቢ ማድረግ፣
16. አትሌቱ በግሉ ለሚፈፅማቸው ህገ ወጥ ድርጊቶች በግል ተጠያቂ ይሆናል፣
17. በአለም አቀፍ ውድድሮች በተመደቡበት ማረፊያ የመግባት እና ከፌዴሬሽኑ የሚሰጠውን ማንኛውም መመሪያ የማክበር፣
18. በአትሌትነቱ ከማንኛውም ወገን ያወቀውን ወይም የተገለፀለትን ሚስጥር የመጠበቅ፣
19. ማንኛውም በብሔራዊ ቡድን የተመረጠ አትሌት ካምፕ ገብቶ ከብሔራዊ ተደመራጭ አትሌቶች ጋር አብሮ የመኖር፣ የመሰልጠንና ተባብሮ የመስራት፣

## አንቀጽ ስምንት
## የአሠልጣኞች መብት

1. አሠልጣኞች ለሥልጠና ሥራቸው የሚያግዟቸው የስፖርት ትጥቆች እስከ መጠቀሚያ መሳሪያዎቹ የማግኘት፣
2. አሠልጣኞች በደረጃቸው ልክ ለሚወጣው የአሠልጣኝነት ማስታወቂያ መወዳደርና በስልጠና ኮርሶች መስፈርቱን ካሟሉ የመወዳደረና የመሳተፍ፣
3. ለሚሰጣቸው ተጨማሪ ሥራ ተገቢ ክፍያ የመጠየቅ፣
4. በፌዴሬሽን ወይም የሥልጠና ኮርሱን ባዘጋጀው አካል አሠልጣኙ ተሳታፊ ከሆነ በኋላ ውጤቱን የሚገልፅ የምስክር ወረቀት የማግኘት፣
5. በወሰደው ኮርስ ብቃቱን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ያለው ማንኛውም አሠልጣኝ ደንቡ በማያዘው መሠረት ለደረጃው ተመጣጣኝ የሆነ የማሰልጠኛ ፈቃድ (License) የማግኘት፣
6. በፌዴሬሽኑ ትዕዛዝ አገልግሎቱን ለመስጠት ወደ ክልል እንዲሁም ተመርጦ ለትምህርትም ሆነ ሙያዊ አገልግሎትን ለማበርከት ከኢትዮጵያ ውጪ ሲንቀሳቀስ በፌዴሬሽኑ መመሪያ መሠረት ማንኛውንም የጉዞ ሰነድ ማሚያ ወጪና የውሎ አበል በጽ/ቤቱ በኩል የማግኘት፣
7. በተመደበበት ሥራ ውሉን ለማቋረጥ ሲፈለግ ከአንድ ወር በፊት የጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ፣
8. በሚቀርብበት አቤቱታ ወይም ክስ ምላሽ የመስጠት፣
9. በመምረጫ መስፈርቱ መሠረት በአለም አቀፍ ውድድሮች የሚሳተፉ አትሌቶች መምረጥ፣

## አንቀጽ ዘጠኝ
## የአሠልጣኞች ኃላፊነት

1. አሠልጣኝነት በየጊዜው የሚሻሻል ዕውቀትን፣ ችሎታንና ክህሎትን የሚጠይቅ መሆኑን ተረድተው በግል ጥረት፣ ልምድን ለመለዋወጥ፣ በስልጠናዎች በመሳተፍና ልዩ ልዩ መንገዶችን በመጠቀም ሙያቸውን የማዳበር፣
2. ሥራቸውን በዕቅድ የመምራትና የመጠቀሚያ መሳሪያዎችን ለየተግባሩ በጥንቃቄ የመጠቀም፣
3. የአሠልጣኝነት ሙያ በሚስጥር እንዲያዝ የሚጠይቃቸውን ሚስጥሮች ሁሉ የመጠበቅ፣
4. በሥነ ምግባራቸውና በብቁ ዜግነትና በአርአያነት ሥራቸውን የማከናወን፣
5. የሙያውን ክብራን ከሚነኩ ድርጊቶች የመታቀብ፣
6. ከብክነትና ከሙስና የፀዳ መሆን፣

7. እራሳቸውን ለለውጥ ዝግጁ በማድረግ፣
8. አሠልጣኞች በስልጠና ላይ እያሉ ለስፖርቱ ዕድገት እንቅፋት ከሚሆኑ ሱሶች እራሳቸውን በመጠበቅ ለሌሎች አርአያ መሆን አለባቸው፣
9. የሙሉ ጊዜ አሠልጣኞች፣ ከብሔራዊ ቡድን ውጪ ሌላ ክለብ ማሰልጠን አይችሉም፣
10. አሠልጣኞች በሚገኘው ውጤት በግልም ሆነ በጋራ የመጠየቅ ኃላፊነት አለባቸው፣
11. አትሌቲክሱን ከሚጎዱ ማናቸውም ተግባራት መቆጠብ አለባቸው፣
12. የአትሌቱን የውድድርና ተገቢ የሆነ የስልጠና መረጃዎችን እንዲሁም ትንተናዎችን ለቴክኒክ ዳይሬክቶሬት ማቅረብ አለባቸው፣
13. ማናቸውም ቅሬታዎች ደረጃውን ጠብቀው እስከ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ድረስ ማቅረብ አለባቸው፣
14. የሚዘዋወሩ አትሌቶችን በህጋዊ መንገድ የመመልመልና የመምረጥ፣

## አንቀጽ አስር
## አሠልጣኞች ከአትሌቶቻቸው ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት

1. ከዘር፣ ከሀይማኖት፣ ከፆታ፣ ከፖለቲካ፣ ከጋብቻ ሁኔታና ከብሔር አድልዎ ነፃ የሆነ አገልግሎት የመስጠት፣
2. ማንኛውም አሠልጣኝ በሌላ ቡድን የታቀፈውን አትሌት ወደ ራሱ ቡድን እንዲገባ ወይም በፌዴሬሽኑ ከተሰጠው አትሌት ውጪ ሌላ አትሌት ወደ ራሱ ቡድን ለማስኮብለል ያለማባበል፣
3. ለአትሌቶቻቸው ተገቢውን አክብሮት የመስጠት፣
4. በአትሌቶቻቸው ላይ ሥነ አዕምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ወሲባዊ ትንኮሳም ይሁን ሌሎች ጉጂ ተፅዕኖዎች ከሥነ ምግባር ውጪ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በህግም የሚያስጠይቅ ድርጊት መሆኑ ታውቆ የመጠንቀቅና በሌሎች እንዳይደርስባቸው የመከላከል፣
5. አትሌቶች ጤንነታቸውና ደህንነታቸውን ከሚጎዱ ሁኔታዎች እንዲጠበቁ ጥረት የማድረግ፣
6. አትሌቶቻቸው ለከፍተኛ ውጤት እንዲበቁ የማበረታታት፣ ጥረታቸውን የማጠናከር፣
7. የእያንዳንዱ አትሌት የውድድር፣ የስልጠና ፍላጎት፣ የአካልና የመንፈስ ጥንካሬ እንዲሁም ማህበራዊ ግንኙነታቸውን በማሳደግ ብቁ ዜጐች እንዲሆኑ የማድረግ፣
8. በአትሌቶች የግል ህይወትና ጉዳይ ከአትሌቶቹ ፈቃድ ውጪ ጣልቃ አለመግባት፣
9. በስልጠና ሂደት ሆነ በውድድር ተግባራት የአትሌቶች ሀሳብና በጐ አመለካከትን የመቀበልና ተሳታፊ እንዲሆኑ የማበረታታት፣
10. ከአትሌቶቻቸው ጋር የሚፈጠሩትን አለመግባባቶች በውይይት በመግባባት መፍታት፣
11. አንድ አሠልጣኝ ለሚያስለጥነው አትሌት የውድድር ህጐችን የማሳወቅ፡፡

## አንቀጽ አስራ አንድ
## አሠልጣኞች ከሙያ ባልደረቦቻቸው ጋር ስላላቸው ግንኙነት

1. የአትሌቱን የስልጠናና የመወዳደር ፍላጐትን ለማዳበር እንዲሁም ለተሻለ ውጤት ለማምጣት አስተዋፅኦ ካላቸው ግለሰቦች ሆነ ድርጅቶች ጋር ሙሉ በሙሉ በትብብር የመስራት፣
2. ከሥራ ባልደረቦቻቸውና ከኃላፊዎቻቸው ጋር ስራን ማዕከል ያደረገ ግልፅ ግንኙነት የመፍጠር፣
3. ከባልደረቦቻቸው ጋር የሚፈጠሩ አለመግባባቶችንና ቅራኔዎችን በውይይትና በመግባባት የመፍታት፣
4. ስለባልደረቦቻቸው የሚኖራቸው ትችት ለሚመለከተው ክፍል ከማሳወቃቸው በፊት በቀጥታ ለችግሩ ባለቤቶች በመጠቆም እንዲታረሙ ጥረት ማድረግ፣
5. አስፈላጊ በሆኑ መድረኮች ሁሉ አሰልጣኞችን የሚገነቡና የሚያሻሽሉ ሙያዊ አስተያየቶችን የማቅረብ፣
6. በማንኛውም መልኩ አለመግባባት ሲፈጠር በህጋዊና በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የመንቀሳቀስ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ አስራ ሁለት
## አሠልጣኞች ከፌዴሬሽኑ ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት

1. በተገቢው መንገድ በሥራ ሰዓትና የስልጠና ቦታ የመገኘት፣
2. በማንኛውም ሰዓት ለፌዴሬሽኑ ቀና ተባባሪና አጋዥ ሆነው የመገኘት፣ ቅሬታ ሲኖርባቸው በጐ ትብብራቸው ሳይቀየር ትክክለኛውን መስመር በመከተል ቅሬታቸውን የማመልከት፣
3. ከፌዴሬሽኑ ጋር የገቡትን ውል የመፈፀም፣ ፌዴሬሽኑ የሚያወጣቸው ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የመፈፀም፣
4. ማንኛውም አሠልጣኝ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ሙያዊ አገልግሎትን ለመስጠት እንዲረዳው ከፌዴሬሽኑ የተረከባቸውን ንብረቶችና ገንዘብ በ10 ቀናት የማወራረድ፣

## አንቀጽ አስራ ሦስት
## አሠልጣኞች ከዳኞችና ከውድድር መሪዎች ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት

1. አሠልጣኞች በውድድር ቦታዎች ሁሉ ዳኞችን የማክበርና የውድድር ህግ ትርጓሜአቸውን መቀበል፣ በውድድር ተግባሩ ላይ የዳኞችን ውሳኔ መቃወም የሚችሉት በቡድን መሪው በኩል ወይም የውድድር ህጉ በሚያዘው መሠረት መከናወን እንዳለበት ማወቅ አለባቸው፣
2. አሠልጣኞች በዳኞች ውሳኔና በህጉ ትርጓሜ ላይ ከተመልካች ህዝብ ጋር አላስፈላጊ ባህሪ አለማሳየት፣

## አንቀጽ አስራ አራት
## አሠልጣኞች ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት

1. ለህብረተሰቡ ከፍተኛ ክብርና ግምት የመስጠት፣ የብሔር ብሔረሰበና ህዝቦችን እኩልነት የማክበር፣
2. ለሀገራቸውና ለህዝባቸው ታማኞች የመሆን፣
3. የዜግነት ግዴታዎቻቸውን የመውጣት፣
4. አሠልጣኞች ለአትሌቱ የውጤት ዕድገት የህብረተሰቡ ድርሻ እንደሚኖር በማመን አክብሮት ማሳየት፣

# ክፍል ሦስት
# የአትሌቶች፣ የአሠልጣኞችና የክለቦች የሥነ-ምግባር ጉድለት ማስተካከያ እርምጃዎችና ደረጃቸው

## አንቀጽ አስራ አምስት
## ስለአትሌቶች የሥነ-ምግባር ጉድለት ማስተካከያ እርምጃዎችና ደረጃቸው

1. አትሌቶች የሥነ-ምግባር ጉድለቶች ሲያሳዩ እንደ ጥፋቱ ዓይነትና መደጋገም ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የሥነ-ምግባር ማስተካከያ እርምጃዎች ይወሰዳል፡፡
   ሀ. በአሠልጣኞችና በቴክኒክ ዳይሬክተሩ በኩል ምክር መስጠት
   ለ. በአሠልጣኞችና በቴክኒክ ዳይሬክተሩ የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠት
   ሐ. በቴክኒክ ኮሚቴ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት
   መ. አትሌቱ የፈፀመው የሥነ-ምግባር ጉድለት ከፍተኛ ሆኖ ሲገኝና ይህም በቴክኒክ ኮሚቴ ታይቶና ተረጋግጦ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ለስራ አስኪያጅ ኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ ይቀርባል፡፡

2. ከፍተኛ የዲሲፒሊን ጉድለት በፈፀመ አትሌት ላይ የሚወሰዱ የዲሲፒሊን እርምጃዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡
   ሀ. ለሶስት ወር ከማንኛውም ስልጠናና ውድድር መታገድ፣
   ለ. ለስድስት ወር ከማንኛውም ስልጠናና ውድድር መታገድ፣
   ሐ. ለአንድ አመት ከማንኛውም ስልጠናና ውድድር መታገድ፣
   መ. ለሁለት ዓመትና ከዚያም በላይ ከስልጠናና ከውድድር መታገድ፣

3. በምክር የሚታለፍ የሥነ-ምግባር ጉድለቶች
   ሀ.ወደ ስልጠና ስፍራ አርፍዶ መምጣት፣
   ለ.የግል ንፅህናን፣ የልምምድ፣ የውድድር ትጥቅንና የመጠቀሚያን መሳሪያዎች በጥንቃቄ አለመያዝ፣
   ሐ.በሀገር ውስጥ ሆነ በውጭ ሀገር በሚያርፍባቸው ክፍሎች ተገቢውን ጥንቃቄ አለማድረግ፣

4. የቃል ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የሥነ-ምግባር ጉድለቶች
   ሀ. ከላይ በንዑስ አንቀጽ ……. ሥር ከተጠቀሱት አንዱን የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈፅሞ በምክር የታለፈና ተመሳሳይ የሥነ-ምግባር ጉድለት ለሁለተኛ ጊዜ ፈፅሞ ሲገኝ፣
   ለ. አብረውት ከሚሰሩ አትሌቶች ጋር ተግባብቶ ያለመስራት፣
   ሐ. ከአሠልጣኝ ጋር ተግባብቶና ተከባብሮ አለመስራት፣
   መ. ያለፈቃድ ከስልጠና ቦታ መቅረት፣
   ሠ. ከተመደበለት አሠልጣኝ ወይም ከተመደበበት ኘሮግራም ውጪ ከሌሎች ጋር ተቀላቅሎ መስራት፣
   ረ. በውድድር ስፍራዎች ዳኝነት ማወክ፣

5. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የሥነ-ምግባር ጉድለቶች
   ሀ. ከላይ በቁጥር 4 ከሀ-ረ ሥር ከተጠቀሱት አንዱን የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈፅሞ በቃል ማስጠንቀቂያ የታለፈና ያንኑ ወይም ተመሳሳይ የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈፅሞ ሲገኝ፣
   ለ. በሀገር ውስጥ ውድድር አጥጋቢ ባልሆነ ምክንያት አለመሳተፍ፣
   ሐ.ፌዴሬሽኑ በሚያደርጋቸው የውድድር የጉዞ ፎርማሊቲ ማሟላት ጥሪዎችና የውድድር ሽልማቶች ላይ ለመገኘት ፍቃደኛ አለመሆን፣
   መ.በፌዴሬሽኑ ተመድበው ሙያዊ ግልጋሎት በመስጠት ላይ ከሚገኙ ሠራተኞች ጋር ተግባብቶ አለመስራት፣
   ሠ. ፌዴሬሽኑ የሚያወጣቸውን ደንቦችና መመሪያዎች አለማክበር፣

6. ለሦስት ወር ከውድድር የሚያሳግዱ የሥነ-ምግባር ጉድለቶች
   ሀ. ከላይ በቁጥር 5 ከሀ-ሠ ከተጠቀሱት የሥነ-ምግባር ጉድለቶች አንደኛውን ፈፅሞ በፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የታለፈና ያንኑ ተመሳሳይ የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈፅሞ ሲገኝ፣
   ለ. የሚፈለግበትን ክፍያ ማዘግየት ወይም ለመክፈል ፈቃደኛ አለመሆን፣
   ሐ. ሀገርን ለሚወክሉ የውድድር ጥሪዎችና ውድድሮች ላይ ቅድሚያ አለመስጠት፣
   መ. በስልጠና ሆነ በውድድር ሥፍራዎች ሁከት መፍጠርና ፀጥታ ማደፍረስ፣
   ሠ. የአትሌቲክስ ስፖርትን በሚጐዳ ተግባር ላይ መሰማራት የስም ማጥፋት ዘመቻ ማካሄድ፣

7. ለስድስት ወር ከውድድር የሚያሳግድ የሥነ-ሥርዓት ጉድለቶች
   ሀ. ከላይ በቁጥር 6 ከሀ-ሠ ከተጠቀሱት የሥነ-ምግባር ጉድለቶች አንደኛውን ፈፅሞ በሶስት ወር ቅጣት የታለፈና ያንኑ ወይም ተመሳሳይ ጉድለት ፈፅሞ የተገኘ፣
   ለ. ፊርማን መኮረጅ ወይም ሰነድ በመደለዝና በመሰረዝ ለማጭበርበር መሞከር፣
   ሐ. የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴን መዝለፍ ዛቻና ማስፈራራት፣
   መ. ያለ በቂ ምክንያት ለብሔራዊ ቡድን ሲመረጥ ምርጫውን አለመቀበል፣
   ሠ. ያለ በቂ ምክንያት ከብሔራዊ የውድድር ዝግጅት ራስን ማሰናበት፣
   ረ. በአፍሪካ ሻምፒዮና፣ በምስራቅና መካከለኛ ሻምፒዩናዎች ላይ ተመርጦ ያልተሳተፈ፣

8. ለአንድ ዓመት ከውድድር የሚያሳግድ የሥነ-ሥርዓት ጉድለቶች
   ሀ.ከላይ በቁጥር 7 ከሀ-ረ ከተጠቀሱት የሥነ-ምግባር ጉድለቶች አንደኛውን ፈፅሞ በስድስት ወር ቅጣት የታለፈና ያንኑ ወይም ተመሳሳይ የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈፅሞ ሲገኝ፣
   ለ.ሀገር ወክሎ ለውድድር ወደ ውጪ ሀገር ተልኮ ሳይወዳደር የኮበለለና ወደ ሀገሩ ተመልሶ የገባ፣
   ሐ.በተለያዩ የአለም ሻምፒዮናዎች፣ በኦሎምፒክና በመላው የአፍሪካ ጨዋታዎች ተመርጦ ያልተሳተፈ አትሌት፣

9. ሁለት አመት ከስልጠናና ውድድር የሚያሳግድ የሥነ-ሥርዓት ጉድለቶች
   ሀ. ከላይ በቁጥር 8 ከሀ-ሐ ከተጠቀሱት የሥነ-ምግባር ጉድለቶች አንደኛውን ፈፅሞ የተገኘ በአንድ አመት ቅጣት የታለፈና ያንኑ ወይም ተመሳሳይ የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈፅሞ ሲገኝ፣
   ለ. አበረታች ዕፅ ወስዶ በምርመራ የተረጋገጠ ሲሆን፣
10.የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ጉዳዩን ከመረመረ በኂላ የእግድ ቅጣቱን ወደ ገንዘብ ማዛወር ይችላል።

## <u>አንቀጽ አስራ ስድስት</u>
## <u>የአሠልጣኞች የሥነ-ምግባር ጉድለት ማስተካከያ እርምጃዎችና ደረጃቸው</u>

1. የቃል ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የሥነ-ምግባር ጉድለቶች
   ሀ. ሥራን በዕቅድና በጋራ ለመስራት ፈቃደኛ አለመሆን፣
   ለ. በስልጠና ሥራ ውስጥ ሚስጥር መያዝ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዩች አለመጠበቅ፣
   ሐ. መጠጥ ወስዶ በሥልጠና ቦታ መገኘት፣

2. የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የሥነ-ምግባር ጉድለቶች
   ሀ. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 9.1 ከሀ-ሐ ከተጠቀሱት የሥነ-ምግባር ጉድለቶች አንዱን ፈፅሞ በማስጠንቀቂያ የታለፈና ያንኑ ተመሳሳይ የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈፅሞ ሲገኝ፣
   ለ. ፌዴሬሽኑ የሚያወጣቸውን ደንቦችና መመሪያዎች አለማክበር፣
3. ከብሔራዊ ሥልጠና የሚያሳግዱ የሥነ-ምግባር ጉድለቶች
   ሀ. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 9.2 ከሀ-ለ ሥር ከተጠቀሱት አንዱን ሥነ-ምግባር ፈፅሞ በፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የታለፈና ያንኑ የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈፅሞ ሲገኝ፣
   ለ. በሙስና ተግባር ላይ መሰማራቱ ሲረጋገጥ፣
   ሐ. ፆታዊ ትንኮሳ መፈፀሙ ሲረጋገጥ፣
   መ. የብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ተልዕኮ አዛብቶ መግለፅና የስም ማጥፋት ዘመቻ ሲያካሂድ፣
   ሠ. በስልጠና ስፍራዎች ሁከት መፍጠር ፀጥታን ማደፍረስ፣
   ረ. አበረታች መድኃኒቶችን ለአትሌቶች የሰጠ፣
   ሰ. በተጭበረበረ ማስረጃ ማሰልጠን ከአሠልጣኝነት ያሳግዳል
   ሸ. አትሌቶችን ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ወደየትኛውም አገር ያስኮበለለ ከማሰልጠን ያሳግዳል
   ቀ. የአገሪቱ ህግ ከሚደነግገው ውጭ ከሀገር ውስጥ ገብቶ ስልጠና ላይ ሲሳተፍ ቢገኝት አሠልጣኙን ከማሰልጠን ያሳግዳል፣ ግለሰቡን በአገሪቱ ህግ መሠረት እንዲዳኝ ያደርጋል።
   በ. በአገር ውስጥ የአገር ውስጥ አትሌቶችንም ሆነ የውጭ አትሌቶችን ለሁለተኛ ሀገር ካለህጋዊ ፈቃድ ማሰልጠን አሠልጣኙን ከማሰልጠን ያሳግዳል በአገሪቱ ህግ መሠረት እንዲዳኝ ያደርጋል።

## <u>አንቀጽ አስራ ሰባት</u>
## <u>የክለብ አመራሮች የሥነ-ምግባር ጉድለት ማስተካከያ እርምጃዎችና ደረጃቸው</u>

1. አንድ የክለብ ቡድን መሪ ወይም አሠልጣኝ በውድድር ስፍራዎች ላይ ያልተገባ ፀባይ ካሳየ የቃል ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

2. አንድ የቡድን መሪ ወይም አሠልጣኝ በውድድር ስፍራዎች ላይ ፌዴሬሽኑ የመደባቸውን ዳኞች ያንጓጠጠ ወይም የውድድሩን መንፈስ ለመለወጥ ማንኛውንም ሙከራ ያደረገ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

3. ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ላይ በውድድሩ ስፍራ የተደባደበና ሁከት የፈጠረ አሠልጣኝ ወይም የቡድን ኃላፊ ጥፋቱ በክለቡ እንደተደረገ በመቁጠር ክለቡ እስከ 5,000.00 (አምስት ሺህ ብር) ሊደርስ የሚችል ቅጣት ይወሰንበታል።

4. ለብሔራዊ ቡድን የተመረጠ አትሌት ያላከ ክለብ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

5. የብሔራዊ ፌዴሬሽኑን ደንብና መመሪያ ሳያከብር የቀረ ክለብ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። ይህንኑ ደግሞ ሲፈፅም ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ይቀጣል።

6. ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጀው ውድድሮች ላይ ያለበቂ ምክንያት ሳይሳተፍ የቀረ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። ይህንኑ ደግሞ ሲፈፅም ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ይቀጣል።

<u>ክፍል አራት</u>
<u>ስለ አማተር አገልጋዩች</u>
<u>አንቀጽ አስራ ስምንት</u>
<u>ከአማተር አገልጋዩች የሚጠበቅ ሥነ-ምግባር</u>

1. ማንኛውም አማተር አገልጋይ ወይም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ዙሪያ በግልና በጋራ ተጠያቂ ይሆናል።
2. ማንኛውም አማተር አገልጋይ ወይም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፡-
   ሀ. በመደበኛ የሥራ አስፈፃሚ ስብሰባ መገኘት፤
   ለ. የፌዴሬሽኑን ስምና ዝና የመጠበቅ፤
   ሐ. እርስ በእርስ የመከባበር የመደማመጥና ሀሳብን የሌላውን ባልደረባ ስብዕና ሳይነኩ በቀጥታ መግለፅ፤
   መ. ከፌዴሬሽኑ ሠራተኞች ጋር መልካምና አርአያ ሆኖ መገኘት፤
   ሠ. ለፌፌዴሬሽኑ ልዩ ልዩ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተገዢ መሆን፤
   ረ. ለስፖርታዊ ጨዋነት መርሆዎች መገዛትና አርአያ መሆን
   ሰ. አሉባልታና አሉባልተኞችን መዋጋት፤
   ሸ. ሙስናንና ብልሹ አሠራርን መዋጋት፤
   ቀ. ከክልል ፌዴሬሽኖች ከክለቦች በአጠቃላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ሁልጊዜም ቢሆን መልካም የሆነ የሥራ ግንኙነት እንዲኖር መጣር፤
   በ. የሥራ አስፈፃሚው የሚያወጣውን የሥራና የስብሰባ ኘሮግራም እንዲሁም ሥነ-ሥርዓት ማክበር ይጠበቅበታል።

3. ከላይ የተገለፁትንና ሌሎች የህግ ጥሰቶች ሲያጋጥሙ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚከተለውን እርምጃ ሊወስድ ይችላል።
   ሀ. ለመጀመሪያ ጊዜ የቃል ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤
   ለ. ለሁለተኛ ጊዜ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤
   ሐ. ጥፋቱ ከፍ ያለ ከሆነም የሥራ አስፈፃሚው ገምግሞ እስከ ጠቅላላ ጉባኤ ድረስ አግዶ ለጉባኤ ውሣኔ ያቀርባል፤
   መ. በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔም የመጨረሻ ይሆናል።

4. የጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔ አማተር አገልጋይን ማሰናበት ከሆነ በምትኩ ተጠባባቂ ይተካል ወይም አዲስ በጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣል።

<u>ክፍል አምስት</u>
<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>
<u>አንቀጽ አስራ ዘጠኝ</u>
<u>የክስና አቤቱታ አቀራረብና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት</u>

ማንኛውም በዚህ ደንብ ላይ በተካተቱ ጉዳዩች መሠረት የሚነሳ ክስና አቤቱታ በሚከተለው መንገድ ይከናወናል።
   ሀ. አትሌቱ፣ አሠልጣኙ ወይም ሌላ የሚመለከተው አካል የክስ አቤቱታውን በጽ/ቤቱ አማካይነት በፅሁፍ ለፌዴሬሉ ፅ/ቤት ያቀርባል።
   ለ. ኮሚቴ የቀረበለትን ክስ ከሥነ-ምግባር ደንቡና ከፌዴሬሽኑ መመሪያዎች ጋር በማገናዘብ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ሁለቱን ወገኖች አቅርቦ በጉዳዩ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ያደርጋል።
   ሐ. ኮሚቴው ሁለቱንም ወገኖች አሉኝ የሚሏቸውን መረጃዎች የማዳመጥና የማየት ኃላፊነት አለበት።
   መ. የሁለቱን ወገኖች የክርክር ጭብጦችን በማገናዘብ ውሳኔ ይሰጣል።
   ሠ. በተሰጠው ውሳኔ ላይ ተቃውሞ ያለው አካል ውሳኔውን በፅሁፍ የማግኘትና በ10 ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው የበላይ አካል ይግባኝ የመጠየቅ መብት አለው።
   ረ. ይግባኝ የሚቀርበው በፌዴሬሽኑ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሆኖ በዚሁ አካል የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

<u>አንቀጽ ሃያ</u>
<u>መመሪያውን ስለመተርጐም</u>

በዚህ መመሪያ ላይ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ጉዳዩች ሲያጋጥሙ የብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ የመተርጐም ስልጣን ይኖረዋል።

<u>አንቀጽ ሃያ አንድ</u>
<u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

ይህን መመሪያ ሊሻሻል የሚችለው በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ ነው።

<u>አንቀጽ ሃያ ሁለት</u>
<u>መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ገባኤ ከፀደቀበት ከህዳር 2 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

ብስራት ጋሻው ጠና
የኢ.ት.አት.ፌ. ኘሬዚዳንት

# የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

# የድጋፍና ሽልማት አሠጣጥ መመሪያ

**ክፍል አንድ**
**ጠቅላላ**
**አንቀጽ አንድ**
**አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የድጋፍና ሽልማት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር ሦስት ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ ሁለት**
**አውጭው አካል**

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**አንቀጽ ሦስት**
**ዓላማና አስፈላጊነት**

የክልሎችንና ከተማ አስተዳድሮች እንዲሁም ክለቦችን ያማከለ የድጋፍ አሰጣጥ መመሪያ በማስፈለጉና ከዚህ በፊት ሽልማትና ድጋፍን በተመለከተ ወጥ የሆነ መመሪያ ስላልነበረ፣ እንዲሁም በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የአትሌቲክስ ስፖርት ዕድገት ተመጣጣኝና ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ የውድድር መንፈስን ለመፍጠር ይህን መመሪያ ማውጣት አስፈልጓል፡፡

**አንቀጽ አራት**
**ትርጉም**

ድጋፍ ማለት፡ - የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ስፖርቱን ለማሳደግ የሚደረጉ ጥረቶችን ለማገዝ የሚሰጥ የገንዘብ፣ የትጥቅ፣ የሙያና የመሳሰሉት እገዛዎች ማለት ነው፡፡

ሽልማት ማለት፡ - የአትሌቲክስ ስፖርት ባለድርሻ አካላት ማለትም የክልል ፌዴሬሽኖች፣ ክለቦችና ማናጀሮች፣ አሠልጣኞችና አትሌቶች ባስገኙት ውጤት መሠረት በምስክር ወረቀት፣ በገንዘብና ወይም በአይነት የሚሰጥ ሰጦታ ማለት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ድጋፍና ሽልማት አሰጣጥ
## አንቀጽ አምስት
## ለክልል ፌዴሬሽኖች የሚሰጥ ድጋፍና ሽልማት

1. በዚሁ አንቀጽ ቁጥር 3 በተመለከቱት መመዘኛዎች መሠረት ደረጃ በማውጣት የክልል ፌዴሬሽን የብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚወስነው መሠረት የምስክር ወረቀትና የገንዘብ ሽልማት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
2. እንዲሁም ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በዚህ አንቀጽ ቁጥር 3 መመዘኛ መሠረት እንደየደረጃቸው የትጥቅ፣ የሙያና የመሳሰሉት ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡
3. ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ የተገለፁት ሽልማትና ድጋፍ መመዘኛዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡
   ሀ. በክልሉ (ከተማ አስተዳደሩ) የአትሌቲክስ ስፖርት ክለቦች ያቋቋመ 20%
   ለ. በክልሉ የአትሌቲክስ ስፖርት ኘሮጀክት ያቋቋመ 15%
   ሐ. በክልሉ የአትሌቲክስ ስፖርት ባለሙያዎችን ያፈራ 10%
   መ.በብሔራዊ ፌዴሬሽኑ የሚዘጋጃቸው የተለያዩ ውድድሮች ላይ የሚያሳዩት ተሳትፎና የሚያገኙት ውጤት 30%
   ሠ. ክልሉ ለአለም አቀፍ ውድድሮች የሚያበቋቸው አትሌቶች ብዛትና ውጤታቸው
   ረ. ክልሉ (ከተማ አስተዳደሩ) የአትሌቲክስ ስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎተን (ማዕከሎች) የገነባና በባለቤትነት የያዘ 15%

## አንቀጽ ስድስት
## ለክለቦች የሚሰጥ ሽልማትና ድጋፍ

1. በዚሁ አንቀጽ ቁጥር 3 በተመለከቱት መመዘኛዎች መሠረት ደረጃ በማውጣት ለክለቦች የብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚወስነው መሠረት የምስክር ወረቀትና የገንዘብ ሽልማት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
2. እንዲሁም ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በዚህ አንቀጽ ቁጥር 3 መመዘኛ መሠረት እንደየደረጃቸው የትጥቅ፣ የሙያና የመሳሰሉት ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡
3. ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ የተገለፁት ሽልማትና ድጋፍ መመዘኛዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡
   ሀ. ታዳጊ፣ ወጣትና አዋቂ አትሌቶችን የያዘ 30%
   ለ. የክለቦችን መቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ ያሟላ 10%
   ሐ. ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጀው የተለያዩ ውድድሮች ላይ ያላቸው ተሳትፎና የሚያስመዘግቡት ውጤት 35%
   መ. በአለም አቀፍ ውድድር ላይ ያስመረጧቸው አትሌቶች ብዛትና ውጤት 25%

## አንቀጽ ሰባት
## ስለ አትሌቶች ሽልማትና ድጋፍ አሠጣጥ

1. በዚሁ አንቀጽ ቁጥር 3 በተመለከቱት መመዘኛዎች መሠረት ደረጃ በማውጣት ለአትሌቶች የብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚወስነው መሠረት የምስክር ወረቀት፣ በገንዘብና በአይነት ሽልማት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
2. እንዲሁም ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በዚህ አንቀጽ ቁጥር 3 መመዘኛ መሠረት እንደየደረጃቸው የትጥቅና የመሳሰሉት ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡
3. ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ የተገለፁት ሽልማትና ድጋፍ መመዘኛዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-
   ሀ. ሀገርን በመወከል በአለም ሻምፒዮናዎች፣ በኦሎምፒክና በመላው አፍሪካ ጨዋታዎች ውጤታማ የሆኑ አትሌቶች፣

   ለ. ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጀው ዋና ዋና ውድድሮች ላይ ክብረ ወሠን ሲያሻሽሉና ኮከብ አትሌት ሲሆኑ፣ በዓመቱ በIAAF መመዘኛ ላይ በመመስረት ሽልማትና ዕውቅና ይሰጠዋል፡፡

## አንቀጽ ስምንት
## ስለ አሠልጣኞች ሽልማትና ድጋፍ አሰጣጥ

1. በዚሁ አንቀጽ ቁጥር 3 በተመለከቱት መመዘኛዎች መሠረት ደረጃ በማውጣት ለአሠልጣኞች የብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚወስነው መሠረት የምስክር ወረቀት፣ በገንዘብና በአይነት ሽልማት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
2. እንዲሁም ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በዚህ አንቀጽ ቁጥር 3 መመዘኛ መሠረት እንደየደረጃቸው የትጥቅ፣ የሙያና የመሳሰሉት ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡
3. ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ የተገለፁት ሽልማትና ድጋፍ መመዘኛዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡
   ሀ. በአለም ሻምፒዮናዎች፣ በኦሎምፒክ ውድድሮች ላይ ባስገኙት ውጤት፤
   ለ. በአትሌቲክስ ስፖርት ዘርፍ የአትሌቲክስ አሠልጣኞችን ያፈራ፣ ህጋዊና ተቀባይነት ያለው ጥናታዊ ፅሁፍ ሲያዘጋጅና ሲያቀርብ ሽልማት ሊሰጠው ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
## አንቀጽ ዘጠኝ
## መመሪያውን ስለመተርጐም

በዚህ መመሪያ ላይ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ የመተርጐም ስልጣን ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ አስር
## መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ ማሻሻልና መለወጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ አንድ
## መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ ከፀደቀበት ከህዳር 25 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ብስራት ጋሻውጠና
የኢት.አት.ፌ. ፕሬዚዳንት

# የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን
# የአትሌቶች መምረጫ
# እና
# የአሠልጣኞች ደረጃ መስጫ
# መስፈርት መመሪያ

ህዳር 2003
አዲስ አበባ

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ
### አንቀጽ አንድ
### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የአትሌቶች መምረጫና የአሠልጣኞች ደረጃ መስጫ መስፈርት መመሪያ ቁጥር "ሁለት" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ ሁለት

### ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፁ ጉዳዩች ሁለቱንም ፆታዎች የሚያካትቱ ይሆናሉ፡፡

### አንቀጽ ሦስት

### አውጭው አካል

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በተሻሻለው የፌዴሬሽኑ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### አንቀጽ አራት

### ዓላማ

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የሀገሪቱን የአትሌቲክስ ስፖርት ለማሳደግ የሚደረገው ጥረት አትሌቶችን በሀገር ውስጥና በአለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርሱና ተተኪ አትሌቶች በብዛት ማፍራት የሚችሉ አሠልጣኞችን ለማግኘት እንዲሁም በውጭ ሀገርን የሚወክሉ አትሌቶችን ለማግኘት ከአድልኦ የፀዳ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለበት አሠራርን ማምጣት፡፡

### አንቀጽ አምስት

1. በዕድሜ ደረጃ በታዳጊ፣ በወጣቶች እና በአዋቂ በመክፈል እንደየደረጃው ብቁ አትሌቶችን የመመልመያ ስርአት ስላልነበረ፡፡
2. ለአለም አገር አቋራጭ፣ ለአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና፣ ለመላው አፍሪካ ጨዋታዎች፣ ለአለም ታዳጊ ወጣቶች፣ ለኦሎምፒክ እና በተለያዩ አለም አቀፍ ውድደሮች ተሳታፊ የሚሆኑትን አትሌቶች በብቃት በጥራትና በብዛት የሚፈሩበት ስርአት ባለመኖሩ፡፡
3. ፍትሃዊ የሆነ መምረጫ መስፈርት ባለመኖሩ፡፡
4. የአሠልጣኞች ደረጃ መስፈርት ባለመኖሩ ይህን መመሪያ ማውጣት አስፈልጓል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ኢትዮጵያን ወክለው ለውድድር የሚመረጡ አትሌቶች ስለሚመረጡበት መስፈርት

## አንቀጽ ስድስት

## የብሔራዊ ቡድን አትሌቶች ለስልጠና የሚመረጡበት ሂደት.

1. ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ለተለያዩ አለም አቀፍ ውድድሮች ሀገርን በመወከል ተሳታፊ የሚሆኑ አትሌቶችን በብቃት ለማዘጋጀት በሚከተለው ሰንጠረዥ መሠረት ለብሔራዊ ቡድን ይመርጣል፡፡

| ተ.ቁ | የሚመረጡበት ርቀት | የሚመረጡበት የውድድር ዓይነት | የሚመረጡ አትሌቶች ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የአጭር ርቀት ቡድን ከ100ሜ.400ሜ. መሰናክልን ጨምሮ ሲሆን | ብሔራዊ ፌደሬሽኑ በሚያዘጋጀው የክልል ሻምፒዮና ላይ | በታዳጊ በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ-3ኛ የሚወጡ አትሌቶች ሊመረጡ ይችላሉ | |
| | | በኢትዮጵያ ሻምፒዮና ውድድር ላይ | በወጣትና በአዋቂ በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ-3ኛ የሚወጡ አትሌቶች ይመረጣሉ | |
| | | በIAAF “A” እና “B” Category መሠረት በተለያዩ አለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ውጤት ያስመዘገቡ አትሌቶች | በሁለቱም ፆታ በቀጥታ ለብሔራዊ ቡድን ይመረጣሉ | |
| 2. | የመካከለኛ ርቀት ቡድን ከ800ሜ.-1500ሜ | ብሔራዊ ፌደሬሽኑ በሚያዘጋጀው የክልል ሻምፒዮና ላይ | በታዳጊ በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ-3ኛ የሚወጡ አትሌቶች ሊመረጡ ይችላሉ | |
| | | በኢትዮጵያ ሻምፒዮና ውድድር ላይ | በወጣትና በአዋቂ በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ-3ኛ የሚወጡ አትሌቶች ይመረጣሉ | |
| | | በIAAF “A” እና “B” Category መሠረት በተለያዩ አለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ውጤት ያስመዘገቡ አትሌቶች | በሁለቱም ፆታ በቀጥታ ለብሔራዊ ቡድን ይመረጣሉ | |
| 3. | የውርወራ ቡድን አሎሎ፣ መዶሻ፣ ዲስክና ጦር | ብሔራዊ ፌደሬሽኑ በሚያዘጋጀው የክልል ሻምፒዮና ላይ | በታዳጊ በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ-3ኛ የሚወጡ አትሌቶች ሊመረጡ ይችላሉ | |
| | | በኢትዮጵያ ሻምፒዮና ውድድር ላይ | በወጣትና በአዋቂ በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ-3ኛ የሚወጡ አትሌቶች ይመረጣሉ | |
| | | በIAAF “A” እና “B” Category መሠረት በተለያዩ አለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ውጤት ያስመዘገቡ አትሌቶች | በሁለቱም ፆታ በቀጥታ ለብሔራዊ ቡድን ይመረጣሉ | |
| 4. | የዝላይ ቡድን ምድር ዝላይ፣ ከፍታ ዝላይ፣ ስሉስ ዝላይና ምርኩዝ ዝላይ | ብሔራዊ ፌደሬሽኑ በሚያዘጋጀው የክልል ሻምፒዮና ላይ | በታዳጊ በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ-3ኛ የሚወጡ አትሌቶች ሊመረጡ ይችላሉ | |
| | | በኢትዮጵያ ሻምፒዮና ውድድር ላይ | በወጣትና በአዋቂ በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ-3ኛ የሚወጡ አትሌቶች ይመረጣሉ | |
| | | በIAAF “A” እና “B” Category መሠረት በተለያዩ አለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ውጤት ያስመዘገቡ አትሌቶች | በሁለቱም ፆታ በቀጥታ ለብሔራዊ ቡድን ይመረጣሉ | |
| 5. | የረዥም ርቀት ቡድን ከ3000ሜ-10000ሜ. እና መሰናክልን ጨምሮ | ብሔራዊ ፌደሬሽኑ በሚያዘጋጀው የክልል ሻምፒዮና ላይ | በታዳጊ በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ-3ኛ የሚወጡ አትሌቶች ሊመረጡ ይችላሉ | |
| | | በኢትዮጵያ ሻምፒዮና ውድድር ላይ | በወጣትና በአዋቂ በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ-3ኛ የሚወጡ አትሌቶች ይመረጣሉ | |
| | | በIAAF “A” እና “B” Category መሠረት በተለያዩ አለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ውጤት ያስመዘገቡ አትሌቶች | | |
| 6. | የማራቶን ቡድን | የሻ/ል አበበ ቢቂላ ኢንተርናሽናል ውድድር | ከ1ኛ-3ኛ የሚወጡ አትሌቶች በቀጥታ ይመረጣሉ፡፡ | |
| | | በተለያዩ አለም አቀፍ ውድድሮች | 12 አትሌቶች በአመጡት የተሻለ ውጤት ይመረጣሉ፡፡ | |
| 7. | የእርምጃ ቡድን | ብሔራዊ ፌደሬሽኑ በሚያዘጋጀው የክልል ሻምፒዮና ላይ | በታዳጊ በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ-3ኛ የሚወጡ አትሌቶች ሊመረጡ ይችላሉ፡፡ | |
| | | በኢትዮጵያ ሻምፒዮና ውድድር ላይ | በወጣትና በአዋቂ በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ-3ኛ የወጡ አትሌቶች ይመረጣሉ፡፡ | |
| | | በIAAF “A” እና “B” Category መሠረት በተለያዩ አለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ውጤት ያስመዘገቡ አትሌቶች | በሁለቱም ፆታ በቀጥታ ለብሔራዊ ቡድን ይመረጣሉ | |

2. በአለም አቀፍ ውድድር የ “A” (የውድድር ደረጃ “ሀ”) እና “B” (የውድድር ደረጃ “ለ”) Category ሰዓት ኖሯቸው በኢትዮጵያ ሻምፒዮና ውድድር ላይ ከ1-3ኛ ደረጃ ቢወጡም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው ውጤት ብቻ የሚያዝላቸው ሆኖ ቀጥሎ ያሉት ከ4-6ኛ ደረጃ ያላቸው በብሔራዊ ቡድን በቀጥታ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

3. አወዳዳሪው አካል በራሱ መርጦ የጋበዘውን ተጋባዥ አትሌት ከዚህ መመዘኛ ውጪ ሆኖ ሊመረጥ ይችላል፡፡

4. ከላይ በሰንጠረዥ የተገለፀው እና ሌላ የተለየ አሠራር ካጋጠመ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሊያውቀውና ሊያፀድቀው ይገባል።

## አንቀጽ ሰባት
## የውድድር አይነቶች

በብሔራዊ ደረጃ ለውድድር አትሌቶች የሚመረጡት ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት የውድድር አይነቶች ይሆናል።

1. ከዚህ በኋላ በዚህ መመሪያ ውድድር ደረጃ “ሀ” እየተባሉ የሚጠሩ ውድድሮች
   ሀ. የኦሎምፒክ ጨዋታዎች
   ለ. የአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና
   ሐ. የመላ አፍሪካ ጨዋታዎች
   መ. የአፍሪካ አዋቂዎች አትሌቲክስ ሻምፒዮና
   ሠ. የአለም የቤት ውስጥ ውድድር
   ረ. የአለም ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና
   ሰ. የአፍሪካ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና
2. ከዚህ በኋላ በዚህ መመሪያ ውድድር ደረጃ “ለ” እየተባሉ የሚጠሩ ውድድሮች
   ሀ. የአለም አገር አቋራጭ አትሌቲክስ ሻምፒዮና
   ለ. የአለም ግማሽ ማራቶን ውድድር
   ሐ. የአለም እርምጃ ውድድር
3. ከዚህ በኋላ በዚህ መመሪያ ውድድር ደረጃ “ሐ” እየተባሉ የሚጠሩ ውድድሮች
   ሀ. የአለም ታዳጊ ወጣቶች ኦሎምፒክ
   ለ. የአለም ታዳጊ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና
   ሐ. የአፍሪካ ታዳጊ ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና
4. ከዚህ በኋላ በዚህ መመሪያ ውድድር ደረጃ “መ” እየተባሉ የሚጠሩ ውድድሮች
   ሀ. የአፍሪካ ዞን አትሌቲክስ ሻምፒዮና
   ለ. ልዩ ልዩ ከአባል ሃገራት የሚመጡ የውድድር ጥሪዎች

## አንቀጽ ስምንት
## አትሌቶች ለመጨረሻ ውድድር ስለሚመረጡበት መስፈርት

1. ከላይ በአንቀጽ ስድስት (1) ለተጠቀሱት ውድድሮች በሚከተለው መስፈርት መሠረት ኢትዮጵያን የሚወክሉ አትሌቶች ይመረጣሉ።
   ሀ. በዜግነት ኢትዮጵያዊ መሆን አለባቸው
   ለ. ዕድሜው ከ20 አመት በላይ የሆነ
   ሐ. ለኦሎምፒክ ጨዋታዎች እና ለአለም ሻምፒዮና የIAAF እንዲሁም ለመላ አፍሪካ ጨዋታዎች እና ለአፍሪካ አዋቂዎች የአፍሪካን ሚኒማ ያሟሉ፤
   መ. በኢትዮጵያ ሻምፒዮና ውድድር የተሳተፉ
   ሠ. በአለም አቀፍ ውድድር የማይዋዥቅ ተከታታይነት ያለው ሰዓት ያስመዘገበ/ች አትሌት (Performance consistency)
   ረ. ወጣቶች ከሆኑ ተተኪነትን ግምት ውስጥ በማስገባት በአንድ ወይም በሁለት አለም አቀፍ የውድድር ሰአት እንዲሁም በተከታታይ የስልጠና ሂደት ግምገማ ውጤታማነቱ የተረጋገጠ
   ሰ. በአገር ውስጥ በአሠልጣኞች የሚሰጥ የስልጠናን ጫና በመቀበል የሚያሳየው የመለወጥ ብቃት (Over compensation)
   ሸ. በአሠልጣኝ በሚሰጡ የመለያ የሰአት ሙከራዎች
   ቀ. ወቅታዊ ጤንነት ግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል።

2. ከላይ በአንቀጽ ስድስት (2) ለተጠቀሱት ውድድሮች በሚከተለው መስፈርት መሠረት ኢትዮጵያን የሚወክሉ አትሌቶች ይመረጣሉ።
   ሀ. በዜግነት ኢትዮጵያዊ፤
   ለ. ፌዴሬሽኑ በሚካሄድባቸው የማጣሪያ ምርጫ ውድድሮች የተሳተፈ፤

ማለትም፡ -

- የአለም አገር አቋራጭ ሻምፒዮና ላይ ለመካፈል በጃንሜዳ አለም አቀፍ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ መካፈል ግዴታ ሆኖ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ደረጃ የወጡ አትሌቶች ይመረጣሉ፡፡ ሆኖም ልዩ ሁኔታ ሲከሰት የ6ኛ አትሌት ምርጫ በፌዴሬሽኑ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

- የአለም ግማሽ ማራቶን ውድድር ላይ ለመካፈል የሱሉልታ ግማሽ ማራቶን ውድድር ላይ መካፈል ግዴታ ሆኖ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ደረጃ ያገኙ አትሌቶች ይመረጣሉ፡፡ ሆኖም ልዩ ሁኔታ ሲከሰት የ6ኛ ደረጃ አትሌት ምርጫ በፌዴሬሽን ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

- ርምጃ ውድድር የሚመረጡ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በሚደረጉ ውድድሮች ከ1ኛ-3ኛ ደረጃ የወጡ ይሆናል ይህ ካልተገኘ ከቀጣዩ ደረጃ ይመረጣሉ፡፡

3. ከላይ በአንቀጽ ስድስት (3) ለተጠቀሱት ውድድሮች በሚከተለው መስፈርት መሠረት ኢትዮጵያን የሚወክሉ አትሌቶች ይመረጣሉ፡፡
   ሀ. በዜግነት ኢትዮጵያዊ፤
   ለ. በዕድሜ ለታዳጊ እና ለወጣቶች የIAAFን መስፈርት ያሟሉ፤
   ሐ. ለአፍሪካ ታዳጊ እና ወጣቶች ሻምፒዮና የአፍሪካን ሚኒማ ያሟሉ፤
   መ. በዚህ ውድድር 1ኛ እና 2ኛ የወጡ ታዳጊ እና ወጣት አትሌቶች ብቻ ይመረጣሉ፡፡

4. ከላይ በአንቀጽ ስድስት (4) ለተጠቀሱት ውድድሮች የሚሣተፉ አትሌቶችን በወቅቱ የሚመደቡ አሠልጣኞች እና ፌዴሬሽኑ በጋራ ይመረጣሉ፡፡

## ክፍል ሦስት
## የአሠልጣኞች ደረጃ መስፈርት
## አንቀጽ ዘጠኝ
## ስለ ረዳት አሠልጣኝ

1. ረዳት አሠልጣኝ ለመሆን፡ -
   ሀ. ዕድሜ ከ18 አመት በላይ የሆነ
   ለ. በሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ወይም በስፖርት ዲኘሎማ ያለው
   ሐ. የIAAF I Level or II Level አንደኛ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ኮርስ ወስዶ ያለፈ ወይም በሀገር ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ኮርስ የወሰደ
   መ. የእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገርና መፃፍ የሚችል
   ሠ. የዲሲፒሊን ግድፈት የሌለበት
   ረ. ተግባብቶ መስራት የሚችል
   ሰ. ከማንኛውም ሱስ ነፃ የሆነ
   ሽ. የአእምሮ ህመምተኛ ያልሆነ ሊሆን ይገባል፡፡
2. በተራ ቁጥር አንድ የተገለፀውን መስፈርት የሚያሟላ ረዳት አሠልጣኝ፡ -
   ሀ. ጀማሪ አትሌቶችን
   ለ. የትምህርት ቤት ተማሪዎችን
   ሐ. የፕሮጀክት አትሌቶችን ያሰለጥናል

## አንቀጽ አስር
## ስለ አሠልጣኝነት

1. አሠልጣኝ ለመሆን፡ -
   ሀ. በሰውነት ማጎልመሻ ዲግሪ እና ከዚያ በላይ
   ለ. የIAAF III Level ኮርስ ወስዶ ያለፈ ወይም ከ3 ወር በላይ በሀገር ውስጥ ኮርስ የወሰደ

ሐ. በረዳት አሠልጣኝነት ለሁለት አመት የሠራ

መ. የእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገርና መፃፍ የሚችል

ሠ. ካገለገለበት ተቋም ስለ ግል ሁኔታ የሚገልፅ ማስረጃ (*Recommendation*) ማቅረብ የሚችል

ረ. ተግባብቶ መስራት የሚችል

ሰ. የዲሲፒሊን ግድፈት የሌለበት

ሸ. ከማንኛውም ሱስ ነፃ የሆነ

ቀ. የአእምሮ ህመምተኛ ያልሆነ ሊሆን ይገባል፡፡

2. ከላይ በአንቀጽ 6 በተራ ቁጥር 1 የተገለፀውን መስፈርት ያሟላ አሠልጣኝ

ሀ. ክለቦችን

ለ. በብሔራዊ ደረጃ የተመረጡ ታዳጊና ወጣት አትሌቶች

## አንቀጽ አስራ አንድ
## ስለ ም/ዋና አሠልጣኝነት

1.ም/ዋና አሠልጣኝ ለመሆን፡ -

ሀ. ዲግሪና ከዚያ በላይ በሰውነት ማጐልመሻ ትምህርት የወሰደ

ለ. 4ኛ ደረጃ የIAAF አሠልጣኝነት ኮርስ ወስዶ ያለፈ ወይም 5ኛ ደረጃ የIAAF አሠልጣኝነት በኮርስ ወስዶ ያለፈ

ሐ. በአሠልጣኝነት አራት ዓመት የሠራ

መ. ከማንኛውም ሱስ ነፃ የሆነ

ሠ. የዲሲፒሊን ግድፈት የሌለበት

ረ. የእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገርና መፃፍ የሚችል

ሰ. የአእምሮ ህመምተኛ ያልሆነ

ሸ. ከሠራበት ተቋም የግል ሁኔታ የሚገልፅ ማስረጃ (Recommendation) ማቅረብ የሚችል

ቀ. ተግባብቶ መስራት የሚችል ሊሆን ይገባል፡

2. ከላይ በአንቀጽ 7 በተራ ቁጥር 1 ላይ የተገለፁትን መስፈርቶች ያሟላ አሠልጣኝ

ሀ. ብሔራዊ ቡድንን የማሠልጠን

ለ. የብሔራዊ ቡድን አሠልጣኞችን የማስተባበር

ሐ. የስልጠና ዕቅድ በማውጣት ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር አብሮ መስራት የሚችል፡

## አንቀጽ አስራ ሁለት
## ፈቃድ ስለመስጠት ሁለት
## ስለ ዋና አሠልጣኝነት

1.ዋና አሠልጣኝ ለመሆን

ሀ. የትምህርት ደረጃ በአሠልጣኝነት MA or MSC ወይም ከዛ በላይ

ለ. በዋና አሠልጣኝነት ክለብ/ቡድን አሠልጥኖ ውጤታማ የሆነ ለዚሁም ማስረጃ ማቅረብ የሚችል

ሐ. በዋና አሠልጣኝነት በማሠልጠን ከአራት ዓመት በላይ የሠራ

መ. አሠልጣኞችን በማስተማር (ሴሚናር፣ ኮርስ ወዘተ...) ያገለገለ

ሠ. ለአትሌቲክስ እድገት በተለያየ መንገድ አስተዋፅኦ ያደረገ

ረ. የስልጠና ዕቅድና ኘሮግራም በማውጣት ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር ተባብሮ መስራት የሚችል

ሰ. የእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገርና መፃፍ የሚችል

ሸ. ተግባብቶ መስራት የሚችል

ቀ. የዲሲፒሊን ግድፈት የሌለበት

በ. ከማንኛውም ሱስ ነፃ የሆነ

ተ. የአእምሮ ህመምተኛ ያልሆነ ሊሆን ይገባል፡፡

2. ከላይ በአንቀጽ 8 በተራ ቁጥር 1 በተገለፀው መስፈርት ያሟላ አሠልጣኝ

ሀ. የብሔራዊ ቡድን አትሌቶችን

ለ. በኦሎምፒክ በአለም ሻምፒዮና እና ለተለያዩ የአለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የተመረጡ አትሌቶችን

ሐ. የብሔራዊ ቡድን ከፍተኛ ዋና አሠልጣኝ ሊሆን ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሦስት
## ፈቃድ ስለመስጠት

ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች በሚያሟሉ ባለሙያዎች እንደየደረጃቸው የአሠልጣኝነት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይመዘግባል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
## አንቀጽ አስራ አራት
## መመሪያውን ስለመተርጐም

በዚህ መመሪያ ላይ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ጉዳዩች ሲያጋጥሙ የብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ የመተርጐም ስልጣን ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ አስራ አምስት
## መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ የፌዴሬሽኑ ጠቅላላ ጉባኤ ማሻሻልና መለወጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ ስድስት
## መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ ከፀደቀበት ከህዳር 25 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ብስራት ጋሻው ጠና
የኢ.አት.ፌ. ኘሬዚዳንት

# የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

# የአትሌቶች የውጭ ውድድር ጉዞ
# እና
# የአትሌት ማናጀሮች አሠራር
# መመሪያ

ህዳር 2003
አዲስ አበባ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የሀገሪቱን የአትሌቲክስ ስፖርት ለማሳደግና ለማስፋፋት ተልዕኮውን በላቀ ደረጃ ከግብ ለማድረስ በሚደረገው ጥረት አትሌቶቻችን በአለም አቀፍ ውድድር ከፍተኛ ደረጃ እንደደረሱ ተተኪ አትሌቶችን በብዛት ማፍራት ዋነኛ አላማው ነው፡፡

በመሆኑም በብሔራዊ ደረጃም ሆነ በግል በክለብ፣ በክልልና በስልጠና ተቋማት በስልጠና ላይ የሚገኙ አትሌቶችን ከሀገር ውጪ የሚደረግ ውድድር ሥርአትን በተከተለ መንገድ ከህጋዊ ማናጀሮቻቸውና ከድርጅቶች በሚቀርቡ ጥሪዎች መሠረት እንዲፈፀም እንዲሁም የአትሌት ማናጀሮች የአትሌቶችን ዘላቂ ጥቅም እና መብታቸውን አክብረው ለጋራ ተጠቃሚነት የሚፈለግባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻል ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## <u>የአትሌቶች የውጭ ውድድር ጉዞ እና</u>
## <u>የአትሌት ማናጀሮች አሠራር መመሪያ</u>

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ
### አንቀጽ አንድ
### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የአትሌቶች የውጭ ውድድር ጉዞ እና የአትሌት ማናጀሮች አሠራር ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር አራት 2003 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀፅ ሁለት
### አውጭው አካል

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በተሻሻለው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# አንቀጽ ሦስት

## ዓላማና አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ አትሌቶች በአለም አቀፍ ውድድሮች ያላቸው ተሣትፎ እንዲያድግና ውጤታማ እንዲሆን፣ በርካታ ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት፣ የውድድር ልምድ ለማግኘት፣ የአትሌቶች መብት ተጠብቆ ውጤታማ ሆነው የልፋታቸውን ዋጋ ፍትሃዊ በሆነ መልኩ እንዲያገኙ ለማድረግና ለራሳቸውም ሆነ ለሀገራቸው የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ እንዲሁም በፌዴሬሽኑ፣ በአትሌቱና በማናጀሩ መካከል ያለው አሠራር ቀልጣፋ፣ ግልፅና ተጠያቂነት ያለው አሠራር በማስፈን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዲኖር ማስቻል ነው፡፡

# አንቀጽ አራት

## ትርጉም

1. ፌዴሬሽን ማለት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ማለት ነው፡፡
2. አትሌት ማለት በክለቦች፣ በክልሎች፣ በማናጀሮችና በማሠልጠኛ ማዕከላት ታቅፈው የአትሌቲክስ ስፖርትን የሚያዘወትሩና የሚወዳደሩ ስፖርተኞች ማለት ነው፡፡
3. ክለብ ማለት የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማሳደግ አትሌቶችን በማሰባሰብና በማሰልጠን በክለብ ደረጃ ተመዝግበው የሚወዳደሩበት የስፖርት ማህበር ነው፡፡
4. አለም አቀፍ ፌዴሬሽን ማለት የአለም አቀፉ አትሌቲክስ ማህበር ፌዴሬሽን (አይ.አ.ኤ.ኤፍ) ማለት ነው፡፡
5. አትሌቲክስ ማለት የመምና የሜዳ ተግባራት፣ የጐዳና ሩጫና የእርምጃ ውድድር፣ ሀገር አቋራጭ እና የተራራ ሩጫ ውድድር ተግባራት ማለት ነው፡፡
6. አለም አቀፍ ውድድር ማለት ከአንድ የውጭ ሀገር በላይ ተሣታፊ ያለበት ውድድር ማለት ነው፡፡
7. ሀገር አቀፍ ውድድር ማለት ማንኛውም በኢትየጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የሚዘጋጅ ወይም ሌላ በፌዴሬሽኑ ዕውቅና ያለው ውድድር ማለት ነው፡፡
8. ህጋዊ ማናጀር ማለት የአትሌቶች ወኪል በመሆን ከአይ.ኤ.ኤ.አፍ እና ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ህጋዊ ዕውቅና ያለው ማናጀር ማለት ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

# ስለ አትሌቶች የውጭ ውድድር ጉዞ

# አንቀፅ አምስት

## <u>የውድድር አይነቶች /የውድድር ጥሪ/</u>

የውድድር ጥሪ በሚከተለው ሁኔታ ለብሔራዊ ፌዴሬሽኑና ለአትሌቱ ሊቀርብ ይችላል፡፡

1. በአይ.ኤ.ኤ.ኤፍ ዕውቅና ተሰጥቷቸው የሚካሄዱ አህጉራዊና አለም አቀፍ ውድድሮች በፌዴሬሽኑ በኩል ወይም በአትሌቱ በኩል ጥሪው ሲመጣ፣
2. ከተለያዩ አቻ ፌዴሬሽኖች ለፌዴሬሽኑ ወይም ለአትሌቱ የሚቀርቡ የግብዣ ውድድሮች፣
3. ፌዴሬሽኑ በራሱ ተነሣሽነት የሚሣተፍባቸው ሌሎች አለም አቀፍ ውድድሮች፣
4. በአትሌት ማናጀሮች አፈላላጊነት የሚመጡ የውድድር ጥሪዎች ይሆናሉ፡፡

# አንቀጽ ስድስት

## <u>ስለ አሠራር ቅደም ተከተል</u>

1. ከላይ በአንቀጽ 5 (1) (2) (3) የተገለፁት የውድድር ጥሪ አይነቶች ሲመጡ፡ -

ሀ. በአትሌቱ በኩል በቀጥታ ጥሪው ከመጣ አትሌቱ ጥሪውን ለብሔራዊ ፌዴሬሽኑና ለክለቡ ያሣውቃል፡፡

ለ. ብሔራዊ ፌዴሬሽኑም አስፈላጊውን ፎርማሊቲ በማሟላት ፈቃድ ይሰጣል፡፡

ሐ. ፌዴሬሽኑ ለአትሌቱ ክልል፣ ክለብ ወይም ማናጀር አትሌቱ ሀገሩን ወክሎ የሚወዳደር መሆኑን ያሣውቃል፡፡

መ. ጥሪው በፌዴሬሽኑ በኩል ከመጣ ለውድድሩ የሚመጥኑ አትሌቶችን ፌዴሬሽኑ ይመርጣል፡፡

ሠ. የተመረጡትን አትሌቶችን ማንነት ለክልሉ፣ ለክለቡ እና ለአትሌት ማናጀሮች ያሣውቃል፡፡

ረ. ፌዴሬሽኑ አስፈላጊውን ፎርማሊቲ እና ትጥቅ በማሟላት እንዲሁም አሠልጣኝና ቡድን መሪ በመምረጥ ወደ ውድድር ቦታ ይልካል፡፡

ሰ. የአትሌቶች ምርጫን በሚመለከት ካለበት ወቅታዊ ብቃት አንፃር፣ አትሌቱ ወደፊት ያለበትን ቀጣይ ውድድሮች ግምት ውስጥ በሚያስገባ መልኩ ይሆናል፡፡

ሸ. ማንኛውም የክልል ፌዴሬሽን፣ ክለብና የአትሌት ማናጀር ለእነዚህ ሀገራዊ ውድድሮች የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

ቀ. በሀገራዊ ውድድሮችና በሌሎች ውድድሮች መካከል መደራረብ ሲኖር እና ከአትሌቱ የግል ጥቅም ጋር ግጭት የሚፈጠር ከሆነና በአትሌቱ ላይ ላቅ ያለ ጉዳት ያመጣል ተብሎ የሚገመት ሲሆን አትሌቱ በየትኛውም ውድድር ቅድሚያ መስጠት ያለበት መሆኑ በፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈፃሚ የሚወሰን ይሆናል፡፡

በ. በዚህ ውድድር ማለትም በአንቀጽ 5 (1) (2) (3) በተገለፁት ውድድሮች ለመሣተፍ አትሌቱ በክልል ወይም በክለብ ወይም በአትሌት ማናጀር የታቀፈ ሊሆን ይገባል፡፡

2. ከላይ በአንቀጽ 5 (4) በተገለፀው አይነት የውድድር ጥሪ ሲመጣ፡ -

ሀ. ማንኛውም በአትሌት ማናጀሮች የሚመጣ ጥሪ ቢያንስ ከሁለት ሣምንት በፊት ለብሔራዊ ለፌዴሬሽኑ በቀጥታ በደብዳቤ፣ በፋክስ ወይም በኢ.ሜይል መላክ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም ተጋባዥ አትሌቱ የውድድር በግልባጭ እንዲያውቀው መደረግ ይኖርበታል፡፡

ለ. የውድድር ጥሪውም የሚከተለውን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

1. የውድድሩ ቦታ ቀን እና የውድድሩን አይነት፣
2. ለውድድሩ የተጋበዘውን አትሌት ወጪ ማን እንደሚሸፍን፣
3. የአትሌቱን መሄጃና መመለሻ ቀን፣
4. የሚያርፍበትን ሆቴል ወይም ቦታ፣
5. በውድድር የሚገኙ ሽልማቶችንና ጥቅማጥቅሞችን፣
6. የማናጀሩን ወይም የውድድር አዘጋጁን ሙሉ አድራሻ ስልክ፣ ፋክስና ኢ.ሜል የመሳሰሉትን መረጃዎች ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሐ. ተጋባዥ አትሌቱም በብሔራዊ አትሌትነት ያልተመረጠ ከሆነ ከክልሉ ወይም ከክለቡ ወቅታዊ ውጤቱን የሚገልፅ (በአመቱ የውድድር ዘመን) ደብዳቤ ወይም መረጃ ለብሔራዊ ለፌዴሬሽኑ ያቀርባል፡፡

መ. የክልል ፌዴሬሽኑም የአትሌቱን ማንነትና ውጤቱን በማረጋገጥ፣ የጥሪውን ትክክለኛነት በመመርመር በሁለት ቀናት ውስጥ ለብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ምላሽ ይሰጣል፡፡

ሠ. ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ የውድድር ጥሪውን አግባብ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

ረ. ጥሪውንም አስመልክቶ የተጋባዥ አትሌት ክልል እና ክለብ እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

ሰ. ፌዴሬሽኑ ለውድድሩ ፈቃድ ሲሰጥ አትሌት የሚወዳደርበትን ዲስፒሊን፣ የውድድር መደራረቦችን፣ አትሌቱ ያለበትን ሀገራዊ ውድድሮች እና አትሌቱ ከሚያገኘው ጥቅም ጋር በተገናዘበ መልኩ ይሆናል፡፡

ሸ. የመጣው ጥሪ በአትሌቱ፣ በክለቡ፣ በማናጀሩ እንዲሁም በሀገራዊ ውድድሮች መካከል የጥቅም ግጭት ተፈጥሮ በአትሌቱ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ የውድድሩን ጉዞ አስመልክቶ በፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈፃሚ የሚወሰን ይሆናል፡፡

ቀ. ማንኛውም ማናጀር በጥሪው ላይ ከተገለፀው የውድድር አይነት እና ከፌዴሬሽኑ ዕውቅና ውጪ ማወዳደር አይችልም፡፡

በ. ተጋባዥ አትሌቱ ወይም ማኛጀሩ የቡድን መሪ እና አሠልጣኝ ሊመርጡ እና በጉዞው ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን አስቀድሞ በጥሪው ውስጥ የተካተተ ሊሆን ይገባል፡፡

ተ. ማንኛውም አትሌት በጥሪ ወረቀቱ መሠረት የሚስተናገደው በዚህ መመሪያ አባሪ ቁጥር አንድ በተገለፀው መሠረት ውድድር ላይ የተሣተፈና ውጤት ያለው ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

ቸ. የቬተራን አትሌቶችና ነባርና ታዋቂ አትሌቶችን በሚመለከት ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በራሱ ወይም ከክልል ፌዴሬሽን ጋር በመነጋገር ፈቃድ ይሰጣል፡፡

ነ. ማንኛውም የሚላክ የውድድር ጥሪ ከፌዴሬሽኑ ጋር አስቀድሞ በተገባው ውል መሠረትና በዚህ መመሪያ መሠረት ፈቃድ ካለው የአትሌት ማናጀር ወይም ወኪል ጋር ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ውጪ የሚመጣን ጥሪ ፌዴሬሽኑ አያስተናግድም፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለአትሌት ማናጀሮችና የአትሌት ማናጀር ወኪሎች

## አንቀጽ ሰባት

## ስለ አትሌት ማናጀሮች

1. ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ የአትሌት ማናጀር ሆኖ ለመሥራት ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው በቅድሚያ በአለም አቀፍ ፌዴሬሽኑ (በአይ.ኤ.ኤ.ኤፍ) ዕውቅና ያለውና ፈቃድ የተሰጠው ሊሆን ይገባል፡፡
2. ማንኛውም ማናጀር የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የሚያወጣቸውን ደንብና መመሪያ አክብሮ ለመንቀሣቀስ ፈቃደኛ ሆኖ ማገኘት ይኖርበታል፡፡
3. ማንኛውም የአትሌት ማናጀር ከአለም አቀፉ ፌዴሬሽን ያገኘውን ዕውቅና ወይም ፈቃድ በመያዝ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ከፌዴሬሽኑ ጋር የውል ስምምነት ይፈፅማል፡፡
4. የውል ሥምምነቱ ዝርዝር ሁኔታ በፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈፃሚ የሚወሰን ሆኖ በየአመቱ ይታደሣል፡፡
5. የውል ስምምነቱንም ፌዴሬሽኑ ለአለም አቀፍ ፌዴሬሽን (አይ.አ.ኤ.ኤፍ) ለአትሌት ማናጀሩም የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ ስምንት

## የአትሌት ማናጀር መብት፣ ኃላፊነትና ግዴታ

1. ማንኛውም የአትሌት ማናጀር የሚከተለው መብት ይኖረዋል፡፡
   - ሀ. ውጤታማ ናቸው የሚላቸውን ማንኛውም አይነት አትሌቶች መርጦ መያዝ ውል መዋዋል፡፡
   - ለ. ከክለብ ውጪ ያሉ አትሌቶችን መርጦ አሠልጣኝ ቀጥሮ ማሠልጠን ወይም የማሰልጠን ፈቃድ ከብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ካገኘ እራሱ ማሰልጠን፡፡
   - ሐ. የአትሌቶች ማሠልጠኛ ካምፕ ከፌዴሬሽኑ ጋር በመነጋገር የመመሥረት፡፡
   - መ. በአለም አቀፍ ፌዴሬሽን ደንብ መሠረት ከአትሌቶች ኮሚሽን መቀበል፡፡
   - ሠ. የዚህን መመሪያ አንቀጽ 9 መመዘኛ ለሚያሟላ ሰው ውክልና የመስጠት መብት ይኖረዋል፡፡
2. ማንኛውም የአትሌት ማናጀር የሚከተለው ኃላፊነትና ግዴታ ይኖርበታል፡፡
   - ሀ. የአትሌቶችን የውድድር ካላንደር ጠንቅቆ የማወቅና ከብሔራዊ ፌዴሬሽኖች ጋር ተባብሮ የመሥራት ኃላፊነትና ግዴታ
   - ለ. ለሀገራዊ ውድድሮች ቅድሚያ የመስጠት፣
   - ሐ. አትሌቶችን ከተከለከሉ አበረታች መድሐኒቶች የመጠበቅ
   - መ. አትሌቶቹ ከሀገር ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ ጤንነታቸውንና ደህንነታቸውን የመከታተል
   - ሠ. አትሌቱን ወክሎ የሚዋዋላቸው ውሎች አትሌቱ አውቆትና አምኖበት እንዲሆን የማድረግ
   - ረ. ለአትሌቱ የሚከፈሉ ክፍያዎችና ወጪዎችን ከውድድሩ በፊት የማሣወቅ እንዲሁም ለአትሌቱ የሚከፈሉ ክፍያዎችን በ3 ወር ጊዜ ውስጥ የመክፈል
   - ሰ. የአሠልጣኝነት ፈቃድ ሳይኖር ማሠልጠን የለበትም
   - ሸ. ከብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ጋር ያለውን ውል እንዲሁም ፈቃድ ወቅቱን ጠብቆ የማደስ

## አንቀፅ ዘጠኝ

## ስለ ማናጀር ወኪሎች

1. ማንኛውም ማናጀር በሀገር ውስጥ ሥራውን የሚያስተባብርለት ወኪል ሊያደርግ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን የሚወክላቸው ወኪሎች የሚከተለውን መስፈርት ሊያሟሉ ይገባል፡፡
   - ሀ. የእንግሊዝኛ ቋንቋ መፃፍና መናገር የሚችል፤
   - ለ. በወንጀል ያልተከሰሰና ጥሩ ሥነ ምግባር ያለው፤
   - ሐ. ዓለም አቀፍ ፌዴሬሽኖች ማህበር (IAAF) ያወጣውን መመዘኛ የሚያሟላ ሲሆን፤
2. ማንኛውም የአትሌት ማናጀር ውክልና የወሰደ ወኪል በዚህ መመሪያ ስለአትሌት ማናጀር የተገለፁት መብት፣ ኃላፊትና ግዴታዎችን ባሟላ መልኩ ሊንቀሣቀስ ይገባል፡
3. በውክልና ሠነዱ ከተሠጠው ኃላፊነትና መብት ውጪ መንቀሣቀስ አይኖርበትም፡፡

## ክፍል አራት

በአትሌት ማናጀሮችና ወኪሎቻቸው ሊፈፀሙ ስለሚችሉ ጥፋቶችና ቅጣታቸው

### አንቀፅ አስር

### ስለ ቅጣት

ይህን መመሪያ የታጠሰ ወይም አፈፃፀሙን ያሰናከለ በዚህ መመሪያ መሠረት ይቀጣል፡፡

### አንቀፅ አስራ አንድ

በአትሌት ማናጀሮችና ለወኪሎቻቸው ሊፈፅሙ ስለሚችሉ ጥፋቶች

ሀ. አትሌቱ የተከለከለ አበረታች መድኃኒት እንዲጠቀም የማድረግ

ለ. አትሌቱን ፌዴሬሽኑን ሳያሣውቅ መጀመሪያ ከሀገር ይዞ ከወጣበት ውጪ በተደጋጋሚ በሌላ ውድድር ላይ ማሳተፍ፡፡

ሐ. የአሠልጣኝነት ፍቃድ ሳይኖር ማሰልጠን

መ. የአትሌቱን ገንዘብ ማጭበርበር

ሠ. ትክክለኛውን የሽልማት መጠን አለማሳወቅ

ረ. ከሥነ-ምግባር ደንቡ በተቃራኒ መንቀሳቀስ

ሰ. ለሀገራዊ ውድድር ለአትሌቶች ፍቃድ መከልከል ወይም የሀሰት ምክንያት ማዘጋጀት

ሸ. አትሌቶችን ማስኮብለል

ቀ. ክፍያዎችን በወቅቱ ያለመክፈል

በ. ፍቃድን በወቅቱ ሳያድሱ መቅረትና አትሌቶችን ማወዳደር

ተ. የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከሚያወጣቸው ደንቦች፣ መመሪያዎችና ከአለም አቀፉ ፌዴሬሽን ደንብ ውጪ መንቀሳቀስ

### አንቀፅ አስራ ሁለት

### የቅጣት አይነቶች

እንደጥፋቱ አይነትና ክብደት በብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በሚመለከተው ኮሚቴና በሥራ አስፈፃሚው አማካኝነት የሚከተሉት ቅጣቶች በአጥፊው ላይ ሊጣሉ ይችላሉ፡፡

ሀ. ከ1,000 ዶላር እስከ 20,000 ዶላር የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት

ለ. ከሦስት ወር እስከ ሁለት አመት የሚደርስ የፍቃድ እገዳ

ሐ. የአትሌት ማናጀርነትን ማገድና ውልን መሰረዝ

### አንቀፅ አስራ ሦስት

### ስለ ይግባኝ

ማንኛውም የአትሌት ማናጀር ወይም ወኪል በየደረጃው እስከ ሥራ አስፈፃሚ ብሎም እስከ አለም አቀፍ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን (አይ.ኤ.ኤ.አፍ) ድረስ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

### ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀፅ አስራ አራት

### መመሪያውን ስለመተርጐም

1. በዚህ መመሪያ ላይ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈፃሚ የመተርጐም ስልጣን ይኖረዋል፡፡
2. አማርኛና እንግሊዝኛ ትርጉም የተለያየ በሚሆንበት ጊዜ የአማርኛው ትርጉም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### አንቀፅ አስራ አምስት

### መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

1. ይህ መመሪያ በፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ፊርማ ፀድቆ ለባለድርሻ አካላት በደብዳቤ ከተላከበት ዕለት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡
2. የዚህ መመሪያ የእንግሊዝኛ ትርጉም ለአለም አቀፉ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አይ.ኤ.አ.ኤፍ ይላካል::

### አንቀፅ አስራ ስድስት

### መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ ማሻሻልና መለወጥ ይችላል፡፡

ብስራት ጋሻውጠና

የኢ.አ.ፌ.ፕሬዚዳንት